# የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ርህሩህ፣ተገልጋይ አክባሪ እና ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሱ የጤና አገልግሎት ሰጪዎችየማፍራት አገራዊ ንቅናቄ

## (የማስፈጸሚያ ሰነድ)

Draft

ታህሳስ 2008 ዓም
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ


| ተቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 1 |
| 2 | የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ስነ-ምግባር ሀገራዊ ነበራዊ ሁኔታ ዳሰሳ (SWOT) የሁኔታ ትንተና፣ | 2 |
| 2.1-2.2 | ጠንካራ ጎን ፣ውስንነቶች | 2 |
| 2.3-2.4 | ምቹ ሁኔታዎች፣ሥጋቶች | 3 |
| 3 | ርሀሩሀ፣ ተገልጋይን አክባሪና ሙያዊ ስነ- ምግባር የተላበሰ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የማፍራት ሀገራዊ ንቅናቄ፣ | 4 |
| 3.1-3.1.3 | የሀገራዊ ንቅናቄው ዓላማ፣ዋና ዓላማ፣ዝርዝር ዓላማዎች፣ግብ | 4 |
| 3.2 - 4 | አስፈላጊነት፣የሀገራዊ ንቅናቄው የአፈጻጸም ስልት | 5 |
| 4.1 | አጠቃላይ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ስነ- ምግባር አሰራር ትግበራ ሁኔታ፣ያሉ ችግሮችና፣የመፍትሄ አቅጣጫዎች ሀገራዊ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | 6 |
| 4.1.1 | የነባራዊ ሁኔታ ግምገማ | 6 |
| 4.2 | ተከታታይነት ያላቸው የሲ.አር.ሲ ማስተግበርያ ስልጠናዎች መስጠት | 6 |
| 4.2.1 | በጤና ተቋማት ውስጥ የሙያ ስነ ምግባር ቀጣይነት ማረጋገጥ (ሲአርሲ) | 6-8 |
| 4.3 | የጤና አገልግሎት ሰጪዎች መረጃ አያያዝ ስርዓት በኤሌትሮኒክስ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ፣ | 9 |
| 4.4 | ወደ ጤና ትምህርት ለሚገቡ ተመልማዮች ስለሚገቡበት የሙያ ዘርፍ ምክር መስጠት፣ | 10 |
| 4.5 | የጤና ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት እና ስርአተ ትምህርት በሲአርሲ እንዲቃኝ ማድረግ፣ | 10 |
| 4.5.1- 4.5.2 | መምህራን፣ተማሪዎች | 10 |
| 4.5.3 | ስርአተ ትምህርት | 11 |
| 4.6 | በጤና ሣይንስ ትምህርት ቤቶች ንቅናቄውን ማስተዋወቅና መተግባር፣ | 11 |
| 4.7 | በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ የትምህርት ደረጃዎች የስነ ምግባር ትምህርት ለሚሰጡ መምህራን የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት እና የተማሪ የጤና ክበባት እንዲጠናከሩ መስራት፣ | 12 |
| 4.8 | የሙያ ማህበራት በንቅናቄው የባለቤትነት ድርሻውን እንዲወስዱ ማድረግ፣ | 12 |
| 4.9 | የንቅናቄአምባሳደሮች በመሰየም ንቅናቄውን ማጠናከር | 13 |
| 4.10 | የገፅታ ግንባታ | 13 |
| 4.11 | ምልዓተ ሕዝቡን የንቅናቄው አካል ማድረግ፣ | 14 |
| 4.12 | ከአገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ ተቋማት የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣ | 14 |
| 4.13 | የሲአርሲ ትግበራ ክትትልና ግምገማ ስርዓት፣ | 14 |
| 5 | በሀገራዊ ንቅናቄው ላይ ባለ ድርሻ አካላት ዝርዝር ሚናና ተሳትፎ | 15 |

| ተቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 5.1 | በንቅናቄው የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር | 15 |
| 5.2 | በሀገራዊ ንቅናቄው ላይ የባለ ድርሻ አካላት ሚናና ተሳትፎ፣ | 16 |
| 5.2.1 | የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ | 16 |
| 5.2.2 | የትምህርት ሚኒስቴር | 16 |
| 5.2.2.1 | የፌደራልየትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትርና ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ | 16 |
| 5.2.3 | የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | 17 |
| 5.2.3.1 | የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትርና ሚኒስትር ዴኤታዎች | 17 |
| 5.2.3.2 | የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 17 |
| 5.2.4 | የህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት | 18 |
| 5.2.5 | የህክምና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት | 19 |
| 5.2.6 | ሌሎች ዳይሬክቶሬቶች | 20 |
| 5.2.7 | ለፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር ተጠሪ የሆኑ ኤጀንሲዎች | 20 |
| 5.2.8 | የክልል/የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች | 20 |
| 5.2.9 | የጤና ተቋማት /የግልና የመንግሥት/ | 21 |
| 5.2.10 | ዩኒቨርሲቲዎችና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች | 22 |
| 5.2.11 | የጤና ሙያ ማህበራት | 23 |
| 5.2.12 | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት | 23 |
| 5.2.13 | የህዝብ ክንፍ | 24 |
| 5.2.14 | የተማሪዎች ህብረትና ማህበራት | 24 |
| 5.2.15 | የክልል ትምህርት ቢሮ | 24 |
| 5.2.16 | የህሙማን ማህበራት ካውንስል | 25 |
| 6 | አደረጃጀት | 26 |
| 7 | የካውንስል አባላት ዝርዝር ፣ ሚና እና ተሳትፎ | 27 |
| 7.1 | የአገር አቀፍ ካውንስል አባላት ዝርዝር | 27 |
| 7.2 | የአገር አቀፍ ካውንስል አባላት ሚና እና ተሳትፎ | 27 |
| 7.3 | የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር፤ ሚና እና ተሳትፎ | 28 |
| 7.4 | የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር | 28 |
| 7.5 | የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስልሚናና ተሳትፎ | 29-31 |
| 7.6 | የ ክልል ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር እና ሚናና ተሳትፎ | 32 |

| ተቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 7.7 | የክልል ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር | 32 |
| 7.8 | የክልል ሲአርሲ ካውንስል አባላት ሚናና ተሳትፎ | 32-33 |
| 7.9 | የዞን ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር ሚናና ተሳትፎ | 33 |
| 7.10 | የዞን ሲአርሲ ካውንስል አባላት ሚናና ተሳትፎ | 34-35 |
| 8 | የሲአርሲ ትግበራ አፈፃፀም ማመላከቻ (Indicators) | 36 |
| 9 | የድርጊት መርሀ ግብር | 37-54 |

## 1.መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግና የሕዝቦቿን የጤና ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል ረገድ በግንባር ቀደምነትነት ከሚጠቀሱት ጥቂት የአፍሪካ አገራት መካከል ናት፡፡ ይህ ለውጥ ሊመጣ የቻለው በመንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት፤ ውጤታማ የፖሊሲ አቅጣጫዎች በመኖራቸው፣ የሕዝባችን የጤናው ሥራ ባለቤትነት መሻሻል፣ የጤና ባለሙያዎች ያላሰለሰ ጥረት እና ከአጋር ድርጅቶች በተገኙ ድጋፎች ድምር ውጤት ነው፡፡ ሆኖም ግን በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን የሕዝባችንን የጤና ፍላጎት በተለይም ጥራት ያለው አገልግሎት ከማዳረስ አንፃር በርካታ ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህ  ክፍተቶች የሥራ አካባቢን ለሰራተኛው ምቹና ሳቢ ከማድረግ አንፃር የሚታዩ ክፍተቶች አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም በአመራሩና በጤና ባለሙያዎች ዘንድ የሚታየው የአመለካከት ችግር በተለይም የባለቤትነት እና የአገልጋይነት መንፈስ አለመኖር ከፍተኛ ድርሻውን ይወስዳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ  ህሙማንን/ተገልጋይን ማዕከል ያደረገ የጤና አገልግሎት ሲባል በዋናነት የሚያመለክተው የተሰጠው አገልግሎት ለህሙማን/ለተገልጋዩ የሚገባውን አክብሮት በመለገስ ፣በመንከባከብና ስሜቱን በመካፈል ጭምር ነው፡፡ ርህሩህ ፣ተገልጋይ አክባሪ እና ሙያዊ ስነ-ምግባር የተላበሱ የጤና ባለሙያዎችን የማፍራት አገራዊ ንቅናቄ በሁለተኛው የጤና ትራንስፎርሜሽን  እቅድ በዋናነት ከተቀመጡት አራት የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ አንዱ ሆኗል፡፡ ይህንን የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ለማስፈጸም መንግስትና በየደረጃው ያሉ የጤና አመራሮች ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርጉ ሲሆን ውጤቱም ህሙማን/ተገልጋዩ የህብረተሰብ ክፍል በጤና አገልግሎቱ ጥራት ዙሪያ የሚያነሱአቸውን ቅሬታዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቀልበስ እንደሚያስችል ታምኖበታል፡፡

በመሆኑም ተገልጋዩ ህብረተሰብ በጤና ባለሙያዎች በሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ተገቢውን አገልግሎት አግኝቶ እንዲረካ ለማድረግ ተገልጋይ አክባሪ እና ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሱ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የማፍራት አገራዊ ንቅናቄ የማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የጤና አገልግሎት ሰጪዎችስነ-ምግባር ሀገራዊ ነበራዊ ሁኔታ ዳሰሳ (SWOT) የሁኔታ ትንተና፣

### 2.1ጠንካራ ጎን

- የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ቁጥር እና ስብጥር በየዓመቱ ከፍተኛ ለውጥ በማሣየት ላይ መሆኑ፣
- የተደራጀ የጤና ልማት ሠራዊት እንቅስቃሴ መኖሩ፣
- የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሱ የጤና አገልግሎትን በባለቤትነት የሚመሩ በሙሉ ልብና ቅንነት ህብረተሰቡን እያገለገሉ ያሉ ሞዴል የጤና አገልግሎት ሰጪዎች (የለውጥ ኃይል) በየደረጃው መኖራቸው፣
- የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የሙያ ማህበራት አቅም እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- የጤና ተቋማት ተደራሽነት መሻሻሉ፣
- የመድኃኒት እና የህክምና ግብዐቶች አቅርቦት እየተሻሻለ መሆኑ፣
- በአገሪቱ የተለያዩ የጤና ሪፎርሞችበመተግበር ላይ መሆኑ፣

### 2.2ውሱንነቶች

**በአመለካከት**

- ሁሉም የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የባለቤትነትና የአገልጋይነት መንፈስ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱ፣
- በቁጥር ቀላል የማይባል የጤና አገልግሎት ሰጪዎች በሥራ ገበታ አዘውትረው የማይገኙ መሆኑ፣
- በሥራ ገበታ ቢገኙም የሥራ ሰዓትን በአግባቡ ካለ መጠቀማቸውም በላይ የሥራ ጊዜን የሚያባክኑ መሆኑ፣
- ተገልጋይን በአክብሮት ካለማስተናገድም ባሻገር ማመናጨቅና ለእንግልት መዳረግ፣
- የሙያ ግዴታን አለመወጣትና ለሙያው ሥነ-ምግባር ተገዥ አለመሆን፣
- በድለላ ተግባር በመሰማራት ሕብረተሰቡ በመንግሥት ተቋም ተገቢውን አገልግሎት እንዳያገኝና ለአላስፈላጊ ከፍተኛ እንግልትና ወጪ እንዲዳረግ መደረጉ፣
- የመድኃኒት ብክነትና እና የሕክምና መሣሪያዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረግ እንዲሁም ሆን ብሎ የመጠቀሚያ ጊዜው እንዲያልፍ ማድረግ፣
- በታካሚ ፊት ሌላ የሙያ አጋርን ማንኳሰስ ("እንዴት ይህን ምርመራ/መድኃኒት አዘዘልሽ”)

## በክህሎት

- ለተገልጋዩ ስለ ሕመሙ ተገቢውን ገለፃ/መረጃ እንዲሁም የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አለመስጠት፣
- የሕክምና ዕውቀትንና ክህሎትን በየጊዜው ለማሳደግ እና መሰረታዊ የክህሎት ማነስ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት አለማድረግ፣

## 2.3ምቹ ሁኔታዎች

- የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣
- የሕዝብ ተሣትፎ እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- የህዝቡ የመረዳዳት ባህል የጠነከረ መሆኑ፣
- የህዝቡ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት የማግኘት ፍላጎት እየጨመረ መምጣት፣
- የህዝቡ ጠንካራ የማህበራዊ እሴቶች እና እርስ በእርስ የመረዳዳት ባህል መኖሩ፣
- ሕዝቡ ትክክለኛ የሆነ የህክምና አገልግሎት በማግኘት ረገድ ያለው ንቃተ ህሊና እየተሻሻለ መምጣቱ፣
- የጤና ባለሙያዎች ማኅበራት እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መምጣቱ፣
- የተለያዩ አለም አቀፍ አጋር ድርጅቶች ለጤናው የሙያ ስነ-ምግባር መሻሻል የሚያደርጉት ድጋፍ እየተጠናቀረ እና እያደገ መምጣቱ፣

## 2.4ሥጋቶች

- የባለሙያ ሥራውን መልቀቅ/ በጤና ተቋማት የተሰማራው የባለሙያ ቁጥር አናሳ መሆን፣
- በየጤና ተቋሙ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ጎልቶ መታየት፣
- በጤና ተቋማት ውስጥ መልካም ምሳሌ የሚሆኑ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ቁጥር አናሳ መሆን፣
- የሚከፈለኝ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም አነስተኛ ነው ብሎ መነጫነጭ፣መቆዘምና በሥራ ላይ መለገም፣

## 3.ርህሩህ፣ ተገልጋይን አክባሪና ሙያዊ ስነ- ምግባር የተላበሰ የጤና አገልግሎትሰጪዎችየማፍራትሀገራዊ ንቅናቄ፣

### 3.1 የሀገራዊው ንቅናቄው ዓላማ

#### 3.1.1 ዋና ዓላማ

የዚህ ሀገራዊ ንቅናቄ ዋና አላማ በአገራችን የጤና አገልግሎት ዘርፉ ውስጥ በመንግሥትም ይሁን በግል ተቋማት የሚሠሩ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች( የጤና ባለሙያዎች፤ የጤና ትምህርት መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች) ርህሩህ፤ ታካሚን አክባሪ ፤ሥነ-ምግባር የተላበሱ ህብረተሰቡን አገልጋዮች እንዲሆኑ በማድረግ የጤና አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነትን በማሻሻል የተገልጋይን እርካታ መጨመር ነው፡፡

#### 3.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- ባለሙያዎች በሙያቸው እንዲኮሩ የጤና ሙያም በህብረተሰቡ ዘንድ ተገቢው ክብር እንዲኖረው የተለያዩ ሥልቶችን መተግበር፣
- የአመለካከት ለውጥ በማምጣት የጤና ሙ-ያ ስነ- ምግባር ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- ስለ ጤና፣ ስላለው የጤና አገልግሎት መብት እና ግዴታውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ህብረተሰብና የጤና አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎችን መፍጠር፣
- በተገልጋይና በጤና ባለሙያ መካከል ያለውን ተግባቦትና የመረጃ ፍሰትን (ኮሚኒኬሽን) የተሳለጠ ማድረግ፣
- ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው በሚሠጣቸው የህክምና ውሣኔ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑበትን አሠራርና ባህል ማሣደግ፣

#### 3.1.3 ግብ

- ርህሩህ ተገልጋይን አክባሪ ሥነ-ሥግባር የተላበሱ እና ሕዝባቸውን አገልጋይ የሆኑ የጤና አገልግሎት ሰጪዎችን በማፍራት በጤናው ዘርፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ማሳካት፡፡

### 3.2 አስፈላጊነት

የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ሙያው የሚጠይቀውን ርህራሄን፣ ተገልጋይን ማክበር፣ የሙያ ሥነ-ምግባርን መጠበቅ እና ሕዝቡን በሙሉ ቅንነትና ከልብ ማገልገል እንዲችሉ አገራዊ ንቅናቄ መተግበር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ንቅናቄ ጤና ባለሙያዎች፣ የሙያ ማህበራት እና የሚዲያ አካላት በየደረጃው የሚገኘው አመራር እና ምልዐተ ሕዝቡ በንቃት የሚሣተፉበት ይሆናል፡፡ ይህ ንቅናቄ በተገቢው ትኩረት የሚተገበር ከሆነ የሕዝቡን የአገልግሎት እርካታ እና ጥራት ጥያቄ የሚመልስ ከመሆኑም በላይ ንቅናቄው ስኬታማ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል ፡፡ ንቅናቄው ስኬታማ ይሆናል ተብሎ የታመነው አብዛኛው የጤና ባለሙያ ወደሙያው ሲቀላቀል የተቸገረን ለመርዳት የታመመን የመፈወስ አገልግሎት ለመስጠት ወዶና መርጦ የገባና የሙያ ግዴታውን ለመወጣት ዝግጁነት ያለው ነው ተብሎ ስለሚታሰብም ጭምር ነው፡፡

ርህሩህ፣ ተገልጋይን አክባሪ፣ ሥነ-ሥግባር የተላበሱ እና ሕዝባቸውን አገልጋይ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የማፍራት አገራዊ ንቅናቄ በጤናው ዘርፍ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ወሣኝ ሚና እንደሚጫወት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም መንግሥት፣ የጤና ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት፣ የጤና ባለሙያዎች እና ምልዐተ ህዝቡ የሚሳተፉበት አገራዊ ንቅናቄ እንዲሆን በንቃት መተግበር ይገባናል፡፡ይህ ንቅናቄ ሰሞንኛ ጉዳይ ሆኖ እንዳይቀር ዝርዝር አፈፃፀሙን የሚያሳልጡ አሠራሮችን እና አደረጃጀቶችን በሁሉም ደረጃ በመፍጠር ወደ ሥራ መግባት ይገባናል፡፡

## 4. የሀገራዊ ንቅናቄው የአፈፃፀም ስልት

በጤና አገልግሎት ሙያተኛው፣ አመራሩ እና ምልዓተ ሕዝቡ በያገባኛል መንፈስ የሚንቀሣቀሱበት አሠራር እና ተጠያቂነት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በሙያ ሥነ ምግባራቸውና በአገልግሎታቸው ምስጉን ለሆኑ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ዕውቅና የሚሰጥበት ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡ በጤና ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት እና ስርዓተ ትምህርት በሲ.አር.ሲ እንዲቃኝ በማድረግ ዙሪያ ስራዎች የሚሰሩ ሲሆንተገልጋዩ ማህበረሰብ በጤና አገልግሎት ሂደት ውስጥ መብትና ግዴታውን የሚገነዘብበት ምቹ ሁኔታዎች ለመፍጠር ከዚህ በታች የሚከተሉት የማስተግበሪያ ስልቶች ተቀምጠዋል ፡፡

## 4.1አጠቃላይ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ስነ- ምግባር አሰራር ትግበራ ሁኔታ፣ያሉ ችግሮችና፣የመፍትሄ አቅጣጫዎች ሀገራዊ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ

### 4.1.1 የነባሪዊ ሁኔታ ግምገማ፡-

የተሣካ ንቅናቄን ለመፍጠር በጤና ሥርዓት ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት መገምገም ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ግምገማ በየተቋማቱ ለማደራጀት የተሞከረው የጤና ልማት ሠራዊት፣ ከሕዝብ ክንፍ ጋር የሚደረገው ውይይት በሆስፒታል ሪፎርም የባለሙያዎች በተለይም ከከፍተኛ ጤና ባለሙያዎች ተሳትፎ እና አገልግሎት አሠጣጥ አንፃር የተጠያቂነት ሥርዓቱ በጥልቀት መገምገም ይኖርበታል፡፡ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ሙያቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ ማነቆ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ሊተነተኑ እና በማህበረሰቡ ዘንድ በጤና አገልግሎትና የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ላይ የሚታየውን የተዛባ አስተያየት ነቅሶ ማውጣት ይገባል፡፡ ይህ የማነቆ ትንተና በየደረጃው መፈጸምና በተለዩት ችግሮች ላይ መተማመን ያስፈልጋል፡፡ የጤናው ዘርፍ አመራር ከአድርባይነት መንፈስ ተላቆ የተሟላ ትግል በየደረጃው እንዲፈጠር የግንባር ቀደም ሚናውን ሊወጣ ይገባል፡፡

- ለዚህም የዳሰሳ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት በተለይም በሰራተኛው ዘንድ በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት የተገልጋይ እርካታ እና በሆስፒታሎች አካባቢ ተገልጋይን ከማክበር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በመዳሰስ ከጤና ተቋማት የመግቢያ በር ጀምሮ በሽተኛው ከተቋሙ እስከሚወጣበት ያሉትን ሁኔታዎች መለካትና መዳሰስ፣
- በተመረጡ የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ፈጣን ዳሰሳ ማከናወን፣
- ከዳሰሳው ውጤት የሚሻሻሉ ጭብጦችን መለየት፣
- ዓለም አቀፍ ልምዶችን መቀመር፣
- እያንዳንዱ የጤና ተቋም በተዘጋጀው የዳሰሳ ቼክ ሊስት መሰረት ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ፣

## 4.2 ተከታታይነት ያላቸው የሲ.አር.ሲ ማስተግበርያ ስልጠናዎች መስጠት

### 4.2.1 በጤና ተቋማት ውስጥ የሙያ ስነ ምግባር ቀጣይነት ማረጋገጥ (ሲአርሲ)

በጤና ተቋማት የሚሰጠው አገልግሎት የተገልጋዩን ክብር የጠበቀ፣ ጥራት ያለው፣ ምሉዕና በተሟላ የመረጃ ግንኙነት /ተግባቦት/ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የጤና ሥነ-ምግባር መርሆዎች በማናቸውም ጊዜ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንን ለመከታተል የሚያስችል አደረጃጀት እና አሠራር በየጤና ተቋም ውስጥ መፍጠር ተገቢ ነው፡፡ የሙያ ሥነ-ምግባር ጉዳይ የአመለካከትና የግንዛቤ ማነቆዎችን በመፍታት ሊተገበር ይገባል፡፡ ይህንን ሊያግዝ የሚችል ተከታታይ እና ቀጣይነት ያለው የአመለካከት ትግል የሚደረግባቸው መድረኮች ሊፈጠሩ ይገባል፡፡

ለዚህም በዋነኛነት በየጤና ተቋሙ ያደራጀነውን የለውጥ ሠራዊት እንደ ጥሩ መደላድል መጠቀም ይቻላል፡፡ በያገባኛል መንፈስ እያንዳንዱ የጤና አቅጣጫዎች ሀገራዊዳሰሳ ጥናት ማካሄድባለሙያ በህሙማን አገልግሎት ላይ የሚታየውን የሥነ-ምግባር ጥሰት የሚታገልበት እና የጤና ባለሙያዎች እርስ በርሳቸው የሚተራረሙበት ባህልን መፍጠርና ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡

በየ15 ቀኑ ባለሙያዎች ከጤና ሥነ-ምግባር እና አገልግሎት ጥራት አንፃር የላቀ አፈጻጸም በየጤና ተቋማቸው ለመፍጠር እንዲቻል ሙያዊ ውይይት ቢያንስ ለ1 ሰዓት እንዲያደርጉ የሚያስችሉ መርሀ ግብሮችን መተግበር ይኖርብናል፡፡ በነዚህ መርሀ ግብሮች የጤና አገልግሎት ሰጪዎች በዙር ስለሙያ ሥነ-ምግባር ዝግጅት አድርገው ለሌሎች ባልደረቦቻቸው ገለፃ የሚያቀርቡበት ሁሉም በንቃት የሚሳተፍበት እንዲሆን ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ይህ እንዲሳካም የየተቋሙ አመራር በኃላፊነት ትግበራውን መከታተል ይኖርበታል፡፡ ውይይቶቹ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ወደውስጣቸው ማየት እንዲችሉ የሚያደርጉና በተነሳሽነት እንዲተገበሩት ማድረግ ይገባል፡፡ ለነዚህም በየተቋሙ ሞዴሎችን ማፍራትና በእነሱ አማካይነት ንቅናቄ እንዲፈጠር መሰራት ይኖርበታል፡፡ በአገር ደረጃም ለመርሀግብሩ ማስፈፀሚያ የሚሆን ካሪኩለም ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በተዘጋጀው ጋይድ ላይንና ማኑዋል መሠረት በየተቋሙ ተገቢው ዝግጅት እየተደረገ ውይይቱ ሊቀጥል ይገባል፡፡ የውይይት/ገለፃ/ አቅራቢዎችና ሰልጣኞች በተቋም ኃላፊዎች እየተረጋገጠ ያደረጉት አስተዎጽኦ በተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ (CPD) መመሪያ መሠረት Credit እንዲያዝላቸው ይደረጋል፡፡ ይህ ተከታታይ ውይይት በጤና አልግሎት ዘርፍ እያመጣ ያለው አስተዋጽኦ የታካሚዎችን እርካታ በመለካት ለውጡን የሚከተሉትን ተግባራት በማከናወን ክትትል ይደረጋል፡፡

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ማጠናከር፣
- የጤና ልማት ሰራዊቱ ህዝቡ በሚያቀርበው ርእስ ላይ እንዲሁም ራሳቸው ርእስ እንዲመርጡ በማድረግ እንዲወያዩ ማድረግ፣
- የሙያ ፎረሞች በመልቲ ዲሲፒሊናሪ ቲም በማይቆራረጥ መልኩ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በየዲሲፒሊናቸው በማይቆራረጥ መልኩእንዲኖራቸው በማድረግ(የቀለመው የተደገመ ነው ቢጠፉ) የሙያ ፎረሞች እርስ በእርሳችው የሚማማሩበትና ችግራችን ምንድን ነው የሚለውን በመነጋገር ለሙያችው ጥብቅና እንዲቆሙ ማድረግ፡፡
- መወያያ የሚሆኑ ኬዞችን አዘጋጅቶ ማሰራጨት፣
- የሙያ ስራ ወሰን (Scope of Practice) ተግባራዊነቱን ማጠናከር፣
- በተቋማት ውስጥ የሲ.አር.ሲ ትግበራና ማሻሻያ ኮሚቴ በማቋቋም ተግባራዊ ማድረግ፣
- አርአያ ለሚሆኑ ባለሙያዎች ግልጽና የማያሻማ መስፈርት በማዘጋጀት የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣
- በየተቋማቱ የስነ-ምግባር ማዕከል ማቋቋም ይህም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴን፣የስነምግባር መኮንን ዩኒት እና የጥራት ማረጋገጥ ኮሚቴን ያቀፈ ይሆናል፣
- የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚወክለው አባል የስነ-ምግባር ማዕከሉ ጸሀፊ ይሆናል፣

- የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ከሙያ ስነ-ምግባርና ብቃት ጉድለት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚያይና ተገቢው የማስተካከያ የውሳኔ ሀሳብ ሊያቀርብ የሚችል እንዲሁም የስነ ምግባር ክፍተቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን ምክረ ሀሳቦች የሚያመነጭ ይሆናል፡፡
- ኮሚቴው ከሁሉም የሙያ አይነት የተዋቀረ አባላት እንዲኖረው ይደረጋል፣
- ለጤና አገልግሎት ሰጪዎች ነባርና አዲስ የወጡ ህጎችን ማሳወቅ፣
- የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ለህሙማኑ ማንነቱን እና የስራ ሀላፊነቱን በመግለጽ ከዚህም በላይ ለህሙማኑ በሚታይ መልኩ የደረት ባጅ/ የመስሪያ ቤቱን መታወቂያ እንዲያደርግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ህሙማኑናየጤና አገልግሎት ሰጪዎች የተለያየ ቋንቋ በሚናገሩበት ሁኔታ በህሙማኑና በባለሙያው መካከል የሚደረገውን ውይይት የሚያስተረጉም ባለሙያ መመደብ፣
- ህሙማኑ ስለበሽታው፣ ስለመድኃኒቱ፣ መድኃኒቱ ስለሚያመጣው የጎንዮሽ ጉዳት፣ የሚጠበቁ ውጤቶችንና ሌሎች አማራጭ ህክምናዎች ህሙማኑ በሚረዳው ቋንቋ መረጃ ማግኘቱን ማረጋገጥ፣
- ህሙማን ከጤና ተቋማት ተሽሏቸው ሲወጡ ስለ ሌሎች ቀጣይ ህክምናዎች በሚረዱት ቋንቋ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ህሙማን ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም ለህክምና ሲተላለፉ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች ብቻ መሆናቸውን እና የተላኩበት ምክንያት በህሙማኑ ካርድ ላይ መስፈሩን ማረጋገጥ ፣
- ላኪው የጤና ተቋም ለህሙማኑ የሚያስፈልገውን የህክምና አይነትና ደረጃ መስጠት የማይችል መሆኑን፣
- ህሙማኑ ራሱ ወደ ሌላ ተመሳሳይ ተቋም እንዲዘዋወር ሲጠይቅ ወይም የአእምሮ ችግር ሲኖርበትና በሚያስታምመው ሰው አማካኝነት ወደ ሌላ ተቋም እንዲዘዋወር መጠየቁን፣
- ህሙማኑ ከአካላዊና ስነልቡናዊ ተጽእኖ፣ ችላ መባል፣ ጾታዊ ትንኮሳ፣ የመብት ጥሰትና ብዝበዛ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በህክምና ወቅት የህሙማኑን የግል እና አካላዊ ሚስጥር መጠበቁን ማረጋገጥ፣
- የህሙማኑን የህክምና ሚስጥር መጠበቁን ለማረጋገጥ በህክምና ካርድ ላይ ያሉትን የህሙማኑን መረጃ ከተቋሙ ውጪ ላለ ለሌላ ለማንም ሰው ከሚከተሉት ምክንያቶች በስተቀር አለመስጠት፡-
- ህሙማኑ ራሱ ፍቃድ ሲሰጥ፣
- ህሙማኑ ወደ ሌላ ተቋም የተዛወረ ከሆነና የተዛወረበት ተቋም መረጃ ከጠየቀ፣
- የመረጃው መውጣት አስፈላጊ ከሆነና በህግ ከተፈቀደ፣
- የህሙማኑ ማንነት እንዳይታወቅ ከተደረገ፣
- ህሙማኑ የአገልግሎትና ለሚሰሩለት ፕሮሲጀሮች የዋጋ ተመኑን እንዲያውቅ መደረጉን ማረጋገጥ፣
- ህሙማኑ የህክምና መረጃውን ቅጂ ማግኘት መቻሉን ማረጋገጥ፣
- ህሙማኑ የህክምና ማስረጃ በእንግሊዝኛ ወይንም በአማርኛ ወይንም በአካባቢው ቋንቋ ተዘጋጅቶ መቀበሉን ማረጋገጥ፣

- ህሙማን ያላቸውን አስተያየትና ሀሳብ ያለምንም ፍርሀት ለጤና ተቋሙ ወይንም ቅሬታ ለመቀበል ለተወከለው ባለሙያ እንዲያቀርቡና በአጭር ጊዜ ውስጥ ያለምንም አድሎ ምላሽ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ህሙማን ስለሚሰጣቸው ህክምናና በህክምናው ዙሪያ ስለሚደረጉት የህክምና ለውጦች አብረው ውሳኔ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፣
- የህክምና ባለሙያዎች የሙያ አልባሳታቸውን በአግባቡ መልበሳቸውን፣ የጸጉር እና የሌሎች አካሎቻቸው አያያዝ እንዲሁም ሙያው የሚጠይቀውን ስብዕና መከተላቸውን ማረጋገጥ፣

## 4.3 የጤና አገልግሎት ሰጪዎችመረጃ አያያዝ ስርዓት በኤሌትሮኒክስ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ፣

የጤናውን ሴክተር ዕድገት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማስቀጠል የሰው ሀብት አስተዳደርና አቅም ግንባታ ስራዎች ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ያለው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና መረጃ አያያዝ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ባለመሆኑ በመረጃ የተደገፈ የአቅም ግንባታ ስራዎች ለመስራት ክፍተት ከመፍጠሩ በተጨማሪ ለተለያዩ የህገወጥ ስራዎች በር ከፍተዋል፡፡

በዚህ መሰረት ክፍተቱን ለመሙላትና የተደራጀ የባለሙያዎች መረጃ እንዲኖር ለማድረግ የሚከተሉት ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

- በጤና ቁጥጥር ዘርፍ የተዘጋጀው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሶፍትዌር በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ ማድረግ፣

- በመላ ሀገሪቱ በስራ ላይ የሚገኙ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የሙያ ፈቃድ ከተሰጣቸው ጊዜ ጀምሮ ያላቸው ስነ ምግባር፣ የወሰዱአቸው ስልጠናዎች፣ ያላቸው የስራ ልምድ፣ከሙያ ስነ-ምግባር ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ግድፈቶች እና የመሳሰሉ መረጃዎች በአግባቡ በመመዝገብ የጤና ባለሙያውን አቅም ለማሳደግም ሆነ የጤና አገልግሎት ስርዓቱን ጥራት ለማስጠበቅ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መዘርጋት፣

- መረጃውን በየጊዜው በማደራጀት ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ጋር ተያይዞ የሚቀረፁ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ እንደ ግብአት መጠቀም እንዲሁም ከስነ ምግባርና ብቃት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

## 4.4 ወደ ጤና ትምህርት ለሚገቡ ተመልማዮች ስለሚገቡበት የሙያ ዘርፍ ምክር መስጠት፣

የጤና ሙያ እጅግ አስጨናቂ ግን የህሊና እርካታን የሚያጎናፅፍ ነው፡፡ ገንዘብ በብዛት ከሚገኝባቸው ሥራዎች ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ ክፍያን የሚያስገኝ ቢሆንም ሙያውን ወዶና ፈቅዶ ለገባ ሰው ክብሩን የሰው ልጅ ሕይወት መታደግ እና ለዜጎች ሥቃያቸውን ማስታገስ በገንዘብ የማይለካ የመንፈስ እርካታን ያጎናጽፋል፡፡ ስለሆነም የታመመን መርዳት፣ ስቃይን ማስታገስ፣ የጤና ችግሮችን ለመቅረፍ የአላማ ቁርጠኝነትና ተነሣሽነት ያላቸው ተማሪዎች ወደ ጤና ሣይንስ መስክ መግባታቸውን የሚያረጋገጥ የአመላመል ሥርዓት እንዲፈጠር ከትምህርት ዘርፍ ጋር በቅንጅት የአሠራር ሥርዓት በማበጀት ወደ ከፍተኛ የትምህርተ ተቋም ለሚገቡ ተመልማዮች ስለሚገቡበት የሙያ ዘርፍ ምክር መስጠት፣

## 4.5 የጤና ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት እና ስርአተ ትምህርት በሲአርሲ እንዲቃኝ ማድረግ፣

### 4.5.1 መምህራን

- መምህራንን በሲአርሲ ማብቃትና ለተማሪዎቻቸው አርአያ እንዲሆኑ ለማስቻል ተከታታይ ስልጠናዎች እንዲወስዱ ማድረግና ሻምፒዎንስ የሆኑ መምህራንን እውቅና መስጠት፣
- መምህራን በሲአርሲ ተቃኝቶ በሚዘጋጀው ካሪኩለም ዙሪያ እንዲሰለጥኑና ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በ ጤና ሳይንስ ኮሌጆች የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎችን ከማስተማር ባሻገር ለተገልጋዩ አገልግሎት የሚሰጡ ስለሆነ ትኩረት በመስጠት ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ፣

### 4.5.2 ተማሪዎች

- የ 360 ዲግሪ ምዘና በማድረግ ሻምፒዎንስ የሆኑ ተማሪዎችን እውቅና መስጠት፣
- በተማሪ ክበባት ውስጥ የሲአርሲ ክበባትን በመፍጠር የተሻለ አውቀት እንዲያገኙ ማስቻል፣

### 4.5.3 ስርአተ ትምህርት

- በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለተማሪዎች የሚሰጡ Ethics and professionalism course ካሪኩለምእንዲፈተሽ በማድረግ ወጥ የሆነ ሀገር አቀፍ ካሪኩለም እንዲኖር ማድረግ፣
- በሚቀረጸው በሲአርሲ ካሪኩለም ውስጥ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ማካተት፣
- ሲአርሲን በጤና ሳይንስ ኮሌጆች በሚሰጡ በሁሉም ትምህርቶች እንዲንጸባረቁ ማድረግ፣
- በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያለው የተማሪዎች ተከታታይ ምዘና ስርዓት ከእውቀትና ክህሎት መለካት ባሻገር አመለካከትን (Attiude) መካተቱን ማረጋገጥ፣

### 4.6 በጤና ሣይንስ ትምህርት ቤቶች ንቅናቄውን ማስተዋወቅና መተግባር፣

ከትምህርት ዘርፍ ጋር በመተባበር የጤና ሥነ-ምግባር ጉዳዮች በካሪኩለም ውስጥ በአግባቡ መካተታቸውን ማረጋገጥና በተቀመጠው መሠረት መተግበራቸውን የምንከታተልበት ሥልት ይቀየሳል፡፡ በተጨማሪው ተማሪዎች ሙያቸውን እንዲወዱና እንዲያከብሩ የህዝብ አገልጋይነት መንፈስን እንዲያዳብሩ ተከታታይ ሥራዎችን በየትምህርት ተቋሙ ልንተገብር ይገባል፡፡ በተለይም ተማሪዎች የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን ከሙያቸው ጋር በተያያዘ እንዲፈጽሙ ይደረጋል፡፡ ይህን ለማሳካትም ለተማሪዎች ህብረት እና ከተማሪዎች የጤና ማህበራት ጋር በትብብር ልንሠራ ይገባል፡፡

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን በአገራዊ ንቅናቄው ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣
- ተማሪዎች ሙያቸውን እንዲወዱና እንዲያከብሩ ብሎም ህብረተሰቡን የማገልገል መንፈስ እንዲያዳብሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፡፡ ለዚህም ከተማሪዎች ህብረትና ከህክምና ተማሪዎች ህብረት ጋር በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡
- ከስርአተ ትምህቱ በተጓዳኝ የጤና ክበባትን በማቋቋም ፡-
- ተማሪዎች በበጎ አድራጎት ስራ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ፤ህሙማንን የማማከር ስራ እንዲሰሩ ማድረግ፤የደም ልገሳ ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የርህራሂ መንፈስ እንዲያዳብሩ ማድረግ፡፡
- በሳምንታዊ እረፍቶቻቸው በሆስፒታል የተኙ ህሙማንን እንዲጎበኙና እንዲያማክሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡
- በአመታዊ እረፍቶቻቸው ግብአት በማሰባሰብ እንክብካቤ የሚሹ ህሙማንን የመርዳት ስራ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

## 4.7 በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ የትምህርት ደረጃዎች የስነ ምግባር ትምህርት ለሚሰጡ መምህራን የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት እና የተማሪ የጤና ክበባት እንዲጠናከሩ መስራት፣

- በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው የሲቪክስና የግብረገብ ትምርት እንዲጠናከር ማድረግ፡፡
- በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ የስነ ምግባር ትምህርት ለሚሰጡ መምህራን በሲአርሲ ዙሪያስልጠናዎችን መስጠት፡፡
- የተማሪዎች የጤና ክበባት እንዲጠናከሩ በማድረግ በትርፍ ጊዜያቸው በሽተኞችን እንዲጎበኙና የበጎ አድራጎት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ስለ ጤና ትምህርት መረጃ የሚሰጡ ብሮውሸር፤ቪሲዲ እና ዶክመንታሪ በማዘጋጀት ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በፕራይመሪ የጤና ተቋማት እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በ ፕራይመሪ ሆስፒታሎች ትምህርት እንዲሰጡ ማድረግ፣

## 4.8 የሙያ ማህበራት በንቅናቄው የባለቤትነት ድርሻውን እንዲወስዱ ማድረግ፣

በሀገራችን ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ብዙ የጤና ባለሙያዎች ማህበራት እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ብዙ አዳዲስ ማህበራት እየተቋቋሙ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ግን የማህበራቱ አባላት ብዛት በሀገራችን ካለው የጤና ሙያተኛ ቁጥር ጋር ሲተያይ ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ማህበራቱ ተደራሽነታቸውን እንዲያሰፉና የአባላት ቁጥራቸውን መጨመር እንዲችሉ በየደረጃው ያለው የመንግሥት መዋቅር ተገቢውን ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህ ንቅናቄ ማህበራቱ በዕቅድ የተመሠረተ ድጋፍ የሚሠጡበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ሙያ በተናጠል የዚሁ የሥራ ዳር ድንበር ያለው ቢሆንም ሕክምና በቡድን የሚሠራ ከመሆኑ አንፃር ሁሉም የቡድኑ አካል የተሰጠውን ሀላፊነት በአግባቡ ስለመወጣቱ ቡድናዊ ግምገማና የውይይት ባህል እንዲያዳብር የሙያ ማህበራቱ የበኩላቸውን በጎ ሚና እንዲጫወቱ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን እንዲችሉ ክትትል ይደረጋል፡፡

- የሙያ ስነ-ምግባርና የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ በአባላት መሀል ማስረጽ፣ ለትግበራ የሚያስፈልግ ሀብት ማሰባሰብና ማስተባበር፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣
- በአመታዊ በአላቶቻቸው ላይ የማስተዋወቅ ሰራዎች መስራት፣
- በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች ላይ ሲአርሲ መካተቱን ማረጋገጥ፣
- በሲአርሲ ንቅናቄና አፈጻጸም ላይ ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲሰሩ አባላትን መደገፍ፣
- በተለያዩ ሚዲያዎች እና ማህበራዊ ድህረ ገጾች የማስተዋወቅ ስራ መስራትና የህትመት ስራዎች ውስጥ የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብን ማካተት፣
- አባሎቻቸው የሲአርሲ አርአያ እንዲሆኑ እንዲሰሩ ማድረግ፣

### የንቅናቄአምባሳደሮች በመሰየም ንቅናቄውን ማጠናከር

የዚህ አገራዊ ንቅናቄ እንዲሳካ በአገር ደረጃ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በጤና ተቋም ውስጥ በጥሩ ሥነ ምግባራቸው እና ሕዝብን በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሉ እና በማገልገል ላይ ያሉ የጤና አገልግሎት ሰጭዎች በአምባሣደርነት ሊሰየሙ ይገባል፡፡ በአምባሳደርነታቸው የሚጫወቱትን ሚና በዝርዝር ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግ በጋራ እንዲዘጋጅላቸው ይደረጋል፡፡ የእነዚህን የጤና አገልግሎት ሰጭዎች ተሞክሮ ቀምሮ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ማስተላለፍ ተገቢ ነው፡፡

## 4.10 የገፅታ ግንባታ

በሀገራችን በግልም ይሁን በመንግሥት የጤና ተቋማት በሚፈጠሩ የአገልግሎት ጥራት መጓደል ምክንያት ለብዙ ዓመታት በህብረተሰቡ ዘንድ የነበረው በጤና አገልግሎት ያለው እምነት እየተሸረሸረ ነው፡፡ በተያያዘም ለጤና አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጠው ክበሬታ እንዲሁ እየቀነሰ ነው፡፡ ስለሆነም ህዝቡ በአገልግሎቱ የበለጠ እምነት እንዲያሳድር እና ለጤና አገልግሎት ሰጪዎች ተገቢውን ክብር እንዲሠጥ የህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ሥራዎችን በሰፊው ልንሠራ ይገባል፡፡ በተለይም በዕለት ተዕለት በጤና ባለሙያዎች የሚሠሩ ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት ለህዝቡ ማስተዋወቅ ይገባናል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ምን ያህል እያንዳንዱ የጤና ሙያ ለህዝብ አገልግሎት ወሣኝ እንደሆነ በሚያሣይ መልኩ ሊፈፀም ይገባል፡፡በተጨማሪም የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የጤናተቋማትን የሚጎበኙበት እና ለሙያው ፍቅር እንዲያሣድሩ የተቀናጀ ፕሮግራም በመቅረጽ ቀጥሎ በተቀመጡት አኳኋን እንተገብራለን፡፡

- የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ በመስራትና ንቅናቄውን የማስተዋወቅ ስራ በስፋት በመስራት በህብረተሰቡ እምነት የሚጣልበት የህክምና አገልግሎት በመፍጠር ሕብረተሰቡ የሚያከብረው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች እንዲኖር የማድረግ፡፡
- ለአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች የተቀናጀ ፕሮግራም በመቅረፅ የተመረጡ ሞዴል የጤና ተቋማትን፤የጤና ሳይንስ ኮሌጆችን ፤መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን እንዲጎበኙ በማድረግ ለሙያው ፍላጎት እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡
- ያሉትን የሚዲያ ተቋማት በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራዎች በቋሚነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ በሰፊው እንዲጀመሩ በማድረግ የጤና ባለሙያውን በጎ ገጽታ እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

## 4.11ምልዓተ ሕዝቡን የንቅናቄው አካል ማድረግ፣

የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ሥነ-ምግባርን ጠብቀው አገልግሎት እንዲሠጡ ተገልጋይ ሕዝብ በጤና ላይ ያለውን ግንዛቤ ማሣደግና መብቱንና ግዴታውን የሚያውቅ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ጥራቱን የጠበቀና የተሟላ የጤና አገልግሎት ማግኘት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዜግነት መብት ስለሆነ መብቱን የሚጠይቅና የሚሟገት ማህበረሰብ ለመፍጠር የጤና ልማት ሠራዊ አደረጃጀታችንን በዚህ ዙሪያ በሰፊው ማነቃነቅ ይገባናል፡፡ በየጤና ተቋማቱ የሚካሄደው የህዝብ ክንፍ ስብሰባን ተቋማዊ በሆነ መልኩ በማስኬድ እያንዳንዱ የጤና ተቋም ከሕዝቡ የሚሠጠውን አስተያየት እየወሰደ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻልና የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ርህራሄ የተላበሰ አገልግሎት እንዲሠጡ የሚካሄደውን ንቅናቄ ለማቀጣጠል እንደ ግብአት ለመጠቀም የሚችልበት ቁመና ማድረስ ይጠበቅብናል፡፡ በየጤና ተቋሙ ለታካሚዎች የሚሰጡ የጠዋት የጤና ትምህርቶች ጥራታቸውን እና የታካሚን ክብር በጠበቀ መልኩ መሰጠቱን መቃኘት ይገባል፡፡ በተጨማሪም በየጤና ተቋሙ አስተዳደር ቦርድ ውስጥ የሚሣተፉ የህብረተሰብ ወኪሎችን አቅም በማሣደግ ንቅናቄው በየተቋሙ ሣይቀዛቀዝ መቀጠሉን እንዲከታተሉ ማብቃት ተገቢ ነው፡፡ በጥሩ ሥነ-ምግባር የሚያገለግሉ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች በህብረተሰቡ ዕውቅና እንዲሰጣቸው ማመቻቸትም ይገባናል፡፡እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ ምልአተ ሕዝቡን የሚያሳትፍ ፎረም የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 4.12 ከአገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ ተቋማት የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣

ለንቅናቄው መሳካት ከአገር ውስጥና ከአለም አቀፍ ተቋማት የልምድ ልውውጥና የተሻለ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ጤና ተቋማት እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## 4.13 የሲአርሲ ትግበራ ክትትልና ግምገማ ስርዓት፣

ርህሩህ፣ ተገልጋይ አክባሪና የሙያ ስነ ምግባር የተላበሱ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የማፍራት ሀገራዊ ንቅናቄው በተቀመጠው አቅጣጫ እየተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ የተለያዩ የክትትልና ሪፖርቲንግ ስርዓቶች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

ርህሩህ፣ ተገልጋይ አክባሪና የሙያ ስነ-ምግባር የተላበሱ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ከማፍራት ጎን ለጎን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎችን በመመርመር ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት

- በፌዴራልና በሁሉም ክልሎች ደረጃ ከሙያ ስነ-ምግባርና ብቃት ጉድለት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚያይና ተገቢውን የማስተካከያ የውሳኔ ሀሳብ ሊያቀርብ የሚችል እንዲሁም የስነ-ምግባር ክፍተቶች በዘላቂነት የሚፈቱበት ምክረ ሀሳቦች የሚያመነጭ የጤና አገልግሎት ሰጪዎችስነ- ምግባር ኮሚቴ ይkkማል፣
- በየደረጃው ባሉ ጤና ተkማት ውስጥም ቢሆን በጤናተkሙ ውስጥ የሲአርሲ ፕሮግራሞች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም የሚፈጠሩ ጉድለቶችን በመመርመር እንዲስተካከሉ የሚያደርግ የስነ ምግባር ኮሚቴ በማkkም ተግባራዊ ይደረጋል፣
- በዚህ መልኩ በእያንዳንዱ ተkም ውስጥ የሚገኙ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ርህሩህ፣ ተገልጋይ አክባሪና የሙያ ስነ-ምግባር የተላበሰ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

## 5.በሀገራዊ ንቅናቄው ላይ ባለ ድርሻ አካላት ዝርዝር ሚናና ተሳትፎ

ለዚህ ንቅናቄ መሣካት በንቅናቄው የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትና በጤናው ዘርፍ ያለው አመራር ቁልፍ ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡ በየተቋሙ ያለውን የአፈጻጸም ክፍትተ በመገምገም ዝርዝር ዕቅድ አውጥቶ ወደ ሥራ እንዲገባ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ይህ ለትውልድ የሚተርፍ ንቅናቄን በያገባናል እና በባለቤትነት መንፈስ በንቅናቄው የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትና በጤናው ዘርፍ ያለው አመራር ለስኬቱ መረባረብ ይገባዋል፡፡ ለዚህም የአስፈጻሚ አካላት ሀላፊነትና ድርሻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡

### 5.1 በንቅናቄው የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር

1.የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ
2.የፖለቲካ እና የማህበረሰብ መሪዎች
3.የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
4. የትምህርት ሚኒስቴር
5. ለፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ኤጀንሲዎች
6. የቁጥጥር አካላት
7. የፍትህ አካላት
8. የክልል መንግስታት እና የከተማ መስተዳድር
9. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር
10. የሡብዓዊ መብት ተቋማት
11. የሀይማኖት መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦች

12. የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች
13. የክልል፣የዞንና የወረዳ ትምህርት ቢሮዎች
14. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
15. የጤና ተቋማት /የግልና የመንግሥት/
16. የጤና ሥነ-ምግባር ኮሚቴዎች
17. የጤና ባለሙያዎች ማህበራት
18. የክልል ጤና ቢሮዎች ፡የዞን እና የወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች
19. ምልአተ ህዝቡ
20. የጤናና የህክምና ሳይንስ ተማሪዎች ኅብረት
21. የሚዲያ ተቋማቶች
22. የጤና አገልግሎት ተገልጋዮች
23. የህሙማን ማህበራት

## 5.2 በሀገራዊ ንቅናቄው ላይ የባለ ድርሻ አካላት ሚናና ተሳትፎ፣

### 5.2.1 <u>የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ</u>

- ሀገራዊ ንቅናቄውን ፖለቲካዊ ትርጉም ሰጥቶ መምራት፣
- ሀገራዊ ንቅናቄውን በሚመለከት አመራርና አቅጣጫ መስጠት፣
- የሀገራዊ ንቅናቄውን ትግበራ በየደረጃው በበላይነት ወጥነት ባለው መልኩ መከታተል፣

### 5.2.2 <u>የትምህርት ሚኒስቴር</u>

#### 5.2.2.1 <u>የፌደራልየትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትርና ሚኒስትር ዴኤታዎች</u>

- ሲአርሲ በጤናና የህክምና ሳይንስ ኮሌጆች ካሪኩለም ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ፣
- በሁለም(የግልና የመንግስት) የጤናና የህክምና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች አገራዊ ንቅናቄውን በባላይነት መምራትና ማስተባበር፣
- በሁለም(የግልና የመንግስት) የጤናና የህክምና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች አገራዊ ንቅናቄውንን በባላይነት ወጥነት ባለው መልኩ መቆጣጠርና መገምገም፣
- አገራዊ ንቅናቄውን የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ስራ መስራት፣
- በሁሉም (የግልና የመንግስት) ጤናና የህክምና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የሲአርሲ ካውንስል መቋቋሙን ማረጋገጥ፣
- ከፌደራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር ጋር በመሆን የትግበራ ሰነድ ማዘጋጀት፣

5.2.3 <u>የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>

5.2.3.1 <u>የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትርና ሚኒስትር ዴኤታዎች</u>

- አገራዊ ንቅናቄውን በባለቤትነት መምራት፣
- ለአገራዊ ንቅናቄው አስፈላጊ ግብአቶች መመደብ፣
- አገራዊ ንቅናቄውን ለባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅ፣
- የአገራዊ ንቅናቄውን ትግበራ መከታተል፣

5.2.3.2 <u>የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት</u>

- አገራዊ ንቅናቄውን በማፋጠን ጥራቱን የጠበቀ ሙያዊ ስነ-ምግባር የተላበሰ እና የህዝብ አመኔታን ያገኘ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ክትትል ማድረግ፣
- አገራዊ ንቅናቄውን በአገር አቀፍ ደረጃ ማስተባበር፣
- ርህሩህ፣ተገልጋይ አክባሪ እና ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሱ የጤና ባለሙያዎችን የማፍራት ሂደቱን ማስተባበርና መደገፍ፣
- አገራዊ ንቅናቄውን የሚያስተባብር ኬዝ ቲም ማቋቋም፣
- ለአገራዊ ንቅናቄው በጀት እንዲመደብ ማድረግ፣
- ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በሰነዶቹ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣
- አገራዊ ንቅናቄውን በይፋ ማስጀመር፣
- ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ለባለድርሻ አካላት ማሰራጨት፣
- ንቅናቄውን በየደረጃው ለማውረድ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት፣
- ለሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተጠሪ የሚሆን ቋሚ ኮሚቴ ማቋቋም፣
- የሲአርሲ ኢኒሼቲቭ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በአመት ሁለት ጊዜ ማድረግ፣
- በአመት ሁለት ጊዜ የግምገማ ስብሰባ መጥራትና ውይይት ማድረግ፣
- አመታዊ ሪፖርት ማጠናቀር፣
- ንቅናቄውን ከጤና ባለሙያዎች ቅድመ ስራ ስልጠና ጋር ማቀናጀት፣
- ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ የምክክር እና የስልጠና መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የንቅናቄውን ትግበራ ለባለድርሻ አካላት በየደረጃው እንዲወርድና እንዲፈጸም ማድረግ፣
- ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ በተዘጋጁ ሰነዶች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ መፈተሽና ማሻሻል፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣
- ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ቢሮዎች እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት መስራት፣

### 5.2.4 የህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

- አገራዊ ንቅናቄውን የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ስራ ባሉት ሚዲያና የማህበራዊ ድህረ ገጾች መስራት፣
- በአገራዊ ንቅናቄው ትግበራ ዙሪያ ለዳይሬክቶሬቱ ሰራተኞች፤ለባለድርሻ አካላትና ለጤና ተቋማት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣
- የቋሚ ኮሚቴው አባል የሚሆን ተወካይ መምረጥና መመደብ፣
- የንቅናቄውን እቅድ በህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት አመታዊ እቅድ ውስጥ ማካተትና ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እቅድ ጋር ማቀናጀት፣
- በዳይሬክቶሬቱ ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር ማቀናጀት፣
- ንቅናቄውን በተቀመጡት የሲአርሲ ትግበራ ማመላከቻ(Indicators) እና ማስፈጸሚያ ሰነዶች መተግበርና መከታተል፣
- ሞዴልና ሻምፒዎን በሆኑ የጤና ባለሙያዎች ስራና በጤና ተቋማት ዙሪያ ዶክመንተሪ ፊልም መስራትና ማስተዋወቅ፣
- በንቅናቄው ዙሪያ አገር አቀፋዊ ዝግጅት እና የፓናል ውይይት ማዘጋጀትና መዘገብ፣
- አገርአቀፋዊ የጤና ባለሙያዎች ቀን ማዘጋጀት፣
- በየሶስት ወሩ የሚታተም ጋዜጣዊ መግለጫ ማዘጋጀት፣
- የሲአር ሲን ጅማሬና የነበረበትን ሁኔታ በተመረጡ የጤና ተቋማት ውስጥ ቅድመ ጥናት ማድረግ፣
- በሲአርሲ ንቅናቄ፣ ፕሮግራም፣ ጽንሰ-ሃሳቦች፤ ግቦችና ዓላማዎች ዙሪያ ለሚዲያ ባለሙያዎች የኢሬንቴሽን ዎርክሾፕ ማዘጋጀት፣
- በ ሲአርሲን ፕሮግራም ንቅናቄ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ስፖት ማዘጋጀትና በተደጋጋሚ በሁሉም ሚዲያ ቻናሎች ማሰራጨት፣
- የኤሌክትሮኒክስ፤ የህትመት፤ የማህበረሰብ ድረ-ገጽና የሚኒስትሪው ዌብሳይት በመጠቀም በሲአርሲ ንቅናቄ ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ የሚዲያ ዘመቻ ማከናወን፣
- በጉዳዩ ለህዝቡ የሚዲያ ካምፔይን ለማነሳሳት በሲአርሲ ንቅናቄው ፕሮግራም ትግበራና በአፈጻጸም ሂደት በየሶስት ወሩ ጋዜጣዊ መግለጫ ማዘጋጀት፣
- ጥሩ የንቅናቄው አፈጻጸም ትግበራ ካላቸው ማህበረሰብ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመር፤ ዶኩመንት ማድረግና ወደሌሎች የማህበረሰብ ክፍል ማስፋትና በሚዲያ የማስተዋወቅ ስራ መስራት፣

- የንቅናቄውን የፕሮግራም አፈጻጸም ደረጃ የሚያሳይ የቅድመ እና ድህረ ዶኩሜንተሪ ፊልም ማዘጋጀትና ተደራሽ በሆነ የሚዲያ ቻናል ማዘጋጀት፣
- ለተገልጋዮቻቸው በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር
- በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

## 5.2.5የህክምና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

- የንቅናቄውን አጀንዳ በ ሆስፒታል ሪፎረም ውስጥ ማካተት፣
- አገራዊ ንቅናቄውን በማፋጠን ጥራቱን የጠበቀ ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሰ እና የህዝብ አመኔታን ያገኘ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- የጤና ተቋማትን በተሟላ ሁኔታ በማደራጀት ለጤና ባለሙያዎች ምቹ የስራ ሁኔታን በመፍጠር ንቅናቄው የተሳካ እንዲሆን ማስቻል፣
- የ ቋሚ ኮሚቴው አባል የሚሆን ተወካይ መምረጥና መመደብ፣
- የንቅናቄውን እቅድ በዳይሬክቶሬቱ አመታዊ እቅድ ውስጥ ማካተትና ከሰው ሀብትልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እቅድ ጋር ማቀናጀት፣
- በዳይሬክቶሬቱ ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማቀናጀት፣
- ንቅናቄውን በተቀመጡት የሲአርሲ ትግበራ ማመላከቻ(Indicators) እና ማስፈጸሚያ ሰነዶች መተግበር፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ ሞዴል የሲአርሲ የጤና ተቋማት በየደረጃው እንዲኖሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ ሞዴል የሲአርሲ የጤና ተቋማት መምረጥና እውቅና እንዲሰጣቸው ማቅረብ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠት፣

### 5.2.6ሌሎች ዳይሬክቶሬቶች

- አገራዊ ንቅናቄውን በማፋጠን ጥራቱን የጠበቀ ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሰ እና የህዝብ አመኔታን ያገኘ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ተቀናጅቶ መሥራት፣
- በአገራዊ ንቅናቄው ዙሪያ ለእያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት ሰራተኞች፣ለባለድርሻ አካላትና ለጤና ተቋማት ስልጠና መስጠትና ትግበራውን መከታተል፣
- የ ቋሚ ኮሚቴው አባል የሚሆን ተወካይ መምረጥና መመደብ፣
- የንቅናቄውን እቅድ ከእያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት አመታዊ እቅድ ውስጥ ማካተትና ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እቅድ ጋር ማቀናጀት፣
- በዳይሬክቶሬቱ ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማቀናጀት፣
- ንቅናቄውን በተቀመጡት የሲአርሲ ትግበራ ማመላከቻ (Indicators)ና ማስፈጸሚያ ሰነዶች መተግበር፣
- የሲአርሲን / ንቅናቄውን ጥራት ማስጠበቅ፣
- ለንቅናቄው የሚያሰፈልጉ ግብአት ማሰባሰብ፣
- ለንቅናቄው የሚሆኑ የህግ ማህቀፎች መቅረጽና ማፀደቅ፣
- ንቅናቄውን በተቀመጡት የሲአርሲ ትግበራ ማመላከቻ (Indicators) ና ማስፈጸሚያ ሰነዶች መሰረት በተዋረድ መተግበሩን መከታተል፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

### 5.2.7ለፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር ተጠሪ የሆኑ ኤጀንሲዎች

- አገራዊ ንቅናቄውን በማፋጠን ጥራቱን የጠበቀ ሙያዊ ስነ ምግባር የተላበሰ እና የህዝብ አመኔታን ያገኘ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣
- የኤጀንሲዎቹ ሀላፊዎች የአድቫይዘሪ ካውንስሉ አባል በመሆን በንቃት መሳተፍ፣
- የጤና ሙያ ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ከሲአርሲ ጋር እብሮ እንዲቀናጅ ማድረግ፣
- የመንግስትና የግል የህክምና ተቋማት አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ማድረጋቸውን መከታተል፣መቆጣጠር፣

### 5.2.8የክልል/የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች

- በጤና ቢሮና በጤና ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩት አገልግሎት ሰጪዎች አገራዊ ንቅናቄውን በተመለከተ ስልጠና መስጠት፣
- በጤና ቢሮና ተቋማት ውስጥ የንቅናቄውን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣

- ስለ ንቅናቄው በተቋማት ውስጥ በሚሰጡት የጤና ትምህርትና ሚዲያን በመጠቀም የማሳወቅ ስራ መስራት፣
- የ ቋሚ ኮሚቴው አባል የሚሆን ተወካይ መምረጥና መመደብ፣

- የንቅናቄውን እቅድ ከአመታዊ እቅድ ውስጥ ማካተትና አፈጻጸሙን መከታተል፣
- በጤና ቢሮው ዲፓርትመንቶች ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ከሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እቅድ ጋር ማቀናጀት፣
- የንቅናቄውን የሩብ አመትአፈጻጸም ሪፖርት ለክልሉ የሲአርሲ ካውንስል ማስገባት፣
- በአመት ሁለት ጊዜ በሚዘጋጀው የግምገማ ስብሰባ ላይ መገኘት፣
- ንቅናቄውን በተቀመጡት የሲአርሲ ትግበራ ማመላከቻ (Indicators)ና ማስፈጸሚያ ሰነዶች መተግበር፣
- በስራ ላይ የሚገኙትን ባለሙያዎች ሙያቸውን በአግባቡ መተግበር የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ፣
- በጤና ቢሮው ሞዴልና ሻምፒዎን የሆኑ ባለሙያዎች መምረጥና የንቅናቄው አካል ማድረግ፣
- በየክልሉ አምባሳደሮችን በመምረጥ ንቅናቄውን እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፣
- በየክልሉ አመታዊ የጤና ባለሙያዎች ቀን በማዘጋጀት ሞዴልና ሻምፒዎን የሆኑ ባለሙያዎችና የጤና ተቋማትን መምረጥና እውቅና መስጠት ብሎም መሸለም፣
- ለንቅናቄው የህግ ማእቀፍ እንዲኖረውና እዲተገበር ማድረግ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ- ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

## 5.2.9<u>የጤና ተቋማት /የግልና የመንግሥት/</u>

- በጤና ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩት አገልግሎት ሰጪዎች አገራዊ ንቅናቄውን በተመለከተ ስልጠና መስጠት፣
- በጤና ተቋማት ውስጥ የንቅናቄውን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣
- ስለ ንቅናቄው በተቋማት ውስጥ በሚሰጡት የጤና ትምህርትና ሚዲያን በመጠቀም የማሳወቅ ስራ መስራት፣
- የ ቋሚ ኮሚቴው አባል የሚሆን ተወካይ መምረጥና መመደብ፣
- በተቋም ደረጃ የሲአርሲ አተገባበር ባለቤትና ስፖንሰር ይሆናል፣
- የንቅናቄውን እቅድ ከአመታዊ እቅድ ውስጥ ማካተትና አፈጻጸሙን መከታተል፣
- በጤና ተቋሙ ዲፓርትመንቶች ለንቅናቄው ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ከክልል ጤና ቢሮ እቅድ ጋር ማቀናጀት፣
- የንቅናቄውን የሩብ አመትአፈጻጸም ሪፖርት ለክልሉ የሲአርሲ ካውንስል ማስገባት
- በአመት ሁለት ጊዜ በሚዘጋጀው የግምገማ ስብሰባ ላይ መገኘት፣
- ንቅናቄውን በተቀመጡት የሲአርሲ ትግበራ ማመላከቻ(Indicators) እና ማስፈጸሚያ ሰነዶች መተግበር፣
- በስራ ላይ የሚገኙትን ባለሙያዎች ሙያቸውን በአግባቡ መተግበር የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ፣

- ሞዴልና ሻምፒዮን የሆኑ ባለሙያዎች መምረጥና የንቅናቄው አካል ማድረግ፣
- በጤና ተቋሙ አምባሳደሮችን በመምረጥ ንቅናቄውን እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፣
- በጤና ተቋሙ አመታዊ የጤና ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች ቀን በማዘጋጀት ሞዴልና ሻምፒዮን የሆኑ ባለሙያዎችን መምረጥና እውቅና መስጠት፣
- ለንቅናቄው የሚወጣውን የህግ ማእቀፍ እንዲተገበር ማድረግ፣
- የጤና ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎች የገጽታ ግንባታ ስራ ሚዲያን በመጠቀም መስራት፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወጡ የንቅናቄው ማኑዋሎችና የማስፈጸሚያ ሰነዶችን ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ- ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣
- ማህበረሰቡ በሲአርሲ ንቅናቄ በእኔነት ስሜት እንዲሳተፍ ማድረግ፣

## 5.2.10 ዩኒቨርሲቲዎችና ጤና ሳይንስ ኮሌጆች

- የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ በቅድመ ሥራ የስልጠና ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ፣
- የጤና ሙያ ሰልጣኞች ሙያቸውን እንዲወዱ፣ እንዲያከብሩና የህዝብ አገልጋይነት መንፈስ የተላበሱ ባለሙያዎችን ማፍራት፣
- ለጤና ሙያ ስልጠና ለሚመለመሉ ተማሪዎች የሚወጣ የምልመላ መስፈርት የሲአር ሲን ፅንሰ-ሀሳብ ያካተተ መሆኑን መተግበርና ማረጋገጥ፣
- በሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ላይ የጤና ሙያ መምህራንና ደጋፊ ሰራተኞች ማሰልጠን፣
- በተቋሙ የሲአርሲን አፈፃፀምና ትግበራን ተከታታይነት ያለው ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣
- የሲአር ሲን ዓላማና ጠቀሜታን በሚዲያ ማስተዋወቅ
- ሥራውን በቅርብ የሚከታተልና የኮሚቴ አባል የሚሆን ባለሙያ መመደብ
- የሲአርሲን ማስፈፀሚያ እቅድን ከመደበኛ የተቋም ዕቅድ ጋር በማጣጣም ክትትል ማድረግ፣
- የሲአርሲን ማስፈፀሚያ ሰነድ በተዋረድ ወደ ዲፓርትመንቶች ማውረድ፣
- የአፈፃፀም ሪፖረት በየሩብ ዓመት ለዩኒቨርሲቲ ሲአርሲ ካውንስል ማቅረብና ቀጣይ አቅጣጫ እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረግ የሲአርሲ ስብሰባ ላይ መሳተፍ፣
- በተቀመጠው የአፈፃፀም መለኪያ መሰረት መተግበር፣
- የጤና ባለሙያ ስልጠና ለሚሰጡ መምህራንና ሰራተኞች ሙያቸውን የሚተገብሩበት ምቹ የሥራ ቦታን መፍጠር፣
- ሞዴል የጤና ባለሙያዎች መምህራንን መለየትና በንቅናቄው ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የሲአርሲ አምባሳደሮችን ዕውቅና መስጠትና የንቅናቄው አካል ማድረግ፣
- ዓመታዊ የጤና ባለሙያ ስልጠና ለሚሰጡ መምህራንና ሰራተኞች ቀን በማዘጋጀት የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡና ምሳሌ የሆኑ መምህራንን ዕውቅና መስጠት፣

- ህጋዊ አሰራሮችንና ፍሬም ወርኮች መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
- በተቋም ደረጃ የሲአርሲአተገባበር ባለቤትና ስፖንሰር ይሆናል
- ከጤና ተማሪዎች ህብረት ጋር ስለተፈፃሚነቱ በጋራ መስራት፣
- የሙያ ስነ-ምግባርና የሲአርሲ ትግበራን የሚከታተል ኮሚቴ ማዋቀር፣
- ሁሉም መምህራን የሲአርሲና የሙያ ስነ-ምግባር ሞዴል ስለመሆናቸው ማረጋገጥ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

## 5.2.11 የጤና ሙያ ማህበራት

- የሙያ ስነ-ምግባርና የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ በአባላት መሀል ማስረፅ፣ ለትግበራ የሚያስፈልግ ሀብት ማሰባሰብና ማስተባበር፣
- አባላትን በማስተባበር ለሲአርሲ ተፈፃሚነቱ መሪ ተዋናይ ይሆናሉ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣
- በአመታዊ በአላቶቻቸው ላይ የማስተዋወቅ ስራዎችን ይሰራሉ፣
- የቴክኒክ አማካሪ በመሆን ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች ላይ ሲአርሲን ያካትታሉ፣ ያረጋግጣሉ፣
- በሲአርሲ ንቅናቄና አፈጻጸም ላይ ጥናታዊ ጽሁፎች እንዲሰሩ አባላትን ይደግፋሉ፣
- በተለያዩ ሚዲያና ማህበራዊ ድህረ ገጾች የማስተዋወቅ ስራ መስራትና የህትመት ስራዎች ውስጥ የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ያካትታሉ፣
- በየሙያ ማህበራቸው እጩ የሲአርሲ አምባሰደሮችን ይመርጣሉ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

## 5.2.12መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት

- ለንቅናቄው የቴክኒክ አማካሪ በመሆን ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- የሙያ ስነ-ምግባርና የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ላይ ለባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣሉ፣ ግብዓት ያሰባስባሉ፣ ያስተባብራሉ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ- ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

5.2.13 <u>የህዝብ ክንፍ</u>

- በሲአርሲ አተገባበር ላይ መሳተፍ፣
- ሥነምግባር የተሞላበት አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን መጠቀም፣
- የጤና ባለሙያዎችና ተቋማት ለሚሰጡት አገልግሎት ድጋፍና ክብር መስጠት፣
- ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎትና የውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ተሳታፊ መሆን፣
- በጤና አገልግሎት ሂደት ውስጥ ተገልጋዩ ያልረካበትን ሁኔታ፣ ባለሙያንና ተቋምን የመጠየቅና ለፍትህ አካል የማቅረብ መብትን ማዳበር፣
- ሞዴል የጤና አገልግሎት ሰጭዎች ምርጫ ላይ በንቃት መሳተፍ፣
- የጤና ተቋማትን በእኔነት መንፈስ መደገፍ፣

5.2.14 <u>የተማሪዎች ህብረትና ማህበራት</u>

- አባላትን በሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ሲአርሲን በተለያዩ ሚዲያዎችና ክበባት ማስተዋወቅ፣
- የ ሲአርሲ ካውንስል አባል ሆኖ ማገልገል፣
- ለአባላቶቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ-ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል
- ለሲአርሲእጩ ሞዴል ተማሪዎችን መምረጥና ለዩኒቨርሲቲ/ኮሌጅ ሲአርሲ ካውንስል ማቅረብ፣

5.2.15 <u>የክልል ትምህርት ቢሮ</u>

- የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ በቅድመ ሥራ የስልጠና ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ፣
- በክልሉ ትምህርት ቢሮ ስር በሚገኙ ተቋማት ሥራውን ማስተባበርና መምራት፣
- የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ና አተገባበር በቋሚነት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት
- የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ እና ትግበራን በመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማስተዋወቅ፣
- ለሲአርሲ ማስፈጸሚያ ግብአት ማሰባሰብ፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ- ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

5.2.16 <u>የህሙማን ማህበራት ካውንስል</u>

- የህሙማን ማህበራት በሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ለሥራው ተግባራዊነት የሚያስፈልግ ሀብት ማሰባሰብና ማስተባበር፣
- ህሙማንን ማስተባበርና በንቅናቄ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- ህሙማን መብትና ግዴታቸውን አውቀው ለተግባራዊነቱ መስራታቸውን ማረጋገጥ፣
- ህሙማን ከጤና ባለሙያዎች ጎን በመሆን ለሲአርሲ ትግበራ እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ህሙማን በጤና ተቋማት ውስጥ በሚወሰኑ ውሳኔዎች ውስጥ በህዝብ ክንፍ በኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስተማር፣
- ህሙማን አላግባብ ለተሰጡና ስነምግባር ለጎደላቸው የህክምና አገልግሎቶች መብታቸውን እንዲጠይቁ ማስተማር፣
- ለተገልጋዮቻቸው አገልግሎታቸውን በርህሩህነት፣ተገልጋይ በማክበር እና ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ መስጠትና መከታተል፣

## 6.አደረጃጀት


ዞናል CRC ካውንስል
ወረዳ CRC ካውንስል
ክልላዊየCRC ካውንስል
ብሄራዊየ CRC አማካሪካውንስል
የቀበሌ CRC ካውንስል
ዩኒቨርስቲ/ ጤ.ሳ.ኮ CRC ካውንስል
ምክትልጠቅላይ ሚኒስቴር

## 7. የ ካውንስል አባላት ዝርዝር ፣ ሚና እና ተሳትፎ

### 7.1 የአገር አቀፍ ካውንስል አባላት ዝርዝር

1. የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ--------------------- የካውንስል ሰብሳቢ
2. የትምህርት ሚኒስቴር-------------------------- የካውንስል ምክትል ሰብሳቢ
3. የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር---------------የካውንስል ጸሐፊ

የካውንስል አባላት

4. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የማህበራዊ ዘርፍ ተጠሪዎች
5. የሀይማኖት መሪዎችና ታዋቂ ግለሰቦች
6. ሌሎች የፌደራል መስሪያ ቤቶች
7. የቁጥጥር አካላት፣
8. የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች፣
9. የፍትህ አካላት፣
10. የሥብዓዊ መብት ተቋማት፣
11. የጤና ባለሙያዎች ማህበራት
12. የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር እና ተጠሪ ኤጀንሲዎች
13. የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳ/ት
14. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
15. የህሙማን ማህበራት
16. የምርምር ተቋማት

### 7.2 የአገር አቀፍ ካውንስል አባላት ሚና እና ተሳትፎ

የአገር አቀፍ ካውንስል አባላት ከላይ የተገለጹትን አባላት የሚይዝ ሲሆን የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የካውንስል ሰብሳቢ፣የትምህርት ሚኒስቴር- የካውንስል ምክትል ሰብሳቢ እንዲሁም የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር - የካውንስል ጸሐፊ በመሆን የሚያገለግሉ ሲሆን የአገር አቀፍ ካውንስሉ የአገራዊ ንቅናቄውን በተመለከተ የሚወሰኑ ውሳኔዎችንና አቀጣጫዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ይሰጣል፡

- የአገራዊ ንቅናቄውን ግብ መሳካት ማረጋገጥ፣
- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ ምክርና አቅጣጫ መስጠት፣

- አመታዊና እስትራተጂክ እቅዶችን ማውጣትና ማጽደቅ፣
- ፖሊሲዎችና ህጎች በአግባቡ መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
- በየሩብ አመቱ የአገር አቀፍ ካውንስል አባላት ስብሰባ ማድረግ፣
- የሩብ አመቱን፣ የግማሽ አመትና የአመት የአገራዊ ንቅናቄውን አፈጻጸም መገምገም፣
- ለንቅናቄውን አመታዊ በጀት ማጽደቅ፣
- በየደረጃው ከክልል እና ከዩኒቨርሲቲ ካውንስል የሚመጡ ሪፖርት ማዳመጥና ምላሽ መስጠት፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚከበሩ የሲአርሲ ቀን፤ የአገር አቀፍ አምባሳደሮች ምርጫ እና ስያሜ እንዲሁም ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ምክር መስጠት፣
- የንቅናቄውን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣
- ንቅናቄውን በቋሚነት መቆጣጠርና መገምገም፣
- በንቅናቄው ንቁ ተሳትፎ ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እውቅና እንዲሰጥ ማድረግ፣
- አገራዊ ንቅናቄውን የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ስራ መስራት፣

## 7.3 የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር፤ ሚና እና ተሳትፎ

### 7.4 የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር

1. የዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት----------------------------የካውንስል ሰብሳቢ
2. የተማሪዎች ህብረት ፕሬዘዳንት-------------የካውንስል ምክትል ሰብሳቢ
3. የጤናና ህክምናሳይንስ ኮሌጆች ዲን------------ የካውንስል ጸሐፊ

**የካውንስል አባላት**

4. የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ስነምግባር ኮሚቴ
5. የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲ ሆስፒታል ዳይሬክተሮች
6. የፋኩሊቲ ዲኖች
7. የ ተማሪዎች ክለባት ተጠሪዎች

## 7.5 የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስልሚናና ተሳትፎ

- የአገራዊ ንቅናቄውን ግብ መሳካት ማረጋገጥ፣
- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ምክርና አቅጣጫ መስጠት፣
- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ አመታዊና እስትራተጂክ እቅዶችን ማውጣትና ማፅደቅ፣
- በየሩብ አመቱ የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ሲአርሲ ካውንስል አባላት ስብሰባ ማድረግ፣
- የሩብ አመቱን የግማሽ አመትና የአመት የንቅናቄውን አፈጻጸም መገምገም፣
- ለንቅናቄው አመታዊ በጀት ማጽደቅ፣
- ለካውንስሉ ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚመጡ ሪፖርት ማዳመጥና ምላሽ መስጠት፣
- በየጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ደረጃ ለሚከበሩ የሲአርሲ ቀን፣ የተቋሙ አምባሳደሮች ምርጫ እና ስያሜ ላይ ምክርና ውሳኔ መስጠት፣
- በየጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ደረጃ የንቅናቄውን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣
- በየጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ንቅናቄውን በቋሚነት መቆጣጠርና መገምገም፣
- በንቅናቄው ንቁ ተሳትፎ ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እውቅና እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ንቅናቄውን በሚመለከት ለጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲ ማህበረሰብ አመራርና አቅጣጫ መስጠት፣
- በየጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች ንቅናቄውን በባላይነት መምራት፣
- የአገራዊ ንቅናቄውን ትግበራ በየጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች በባላይነት ወጥነት ባለው መልኩ መቆጣጠር፣
- አገራዊ ንቅናቄውን የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ስራ መስራት፣
- ለጤና ሙያ ስልጠና ለሚመለመሉ ተማሪዎች የሚወጣ የምልመላ መስፈርት የሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

- በሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ ላይ ለጤና ሙያ መምህራንና ደጋፊ ሰራተኞች ስልጠና መሰጠቱን ማረጋገጥ፣
- በተቋሙ የሲአርሲ አፈፃፀምና ትግበራን ተከታታይነት ያለው ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣
- የሲአርሲ ዓላማና ጠቀሜታን ለመምህራንና ተማሪዎች በማህበራዊ ድህረ ገጽና ሚዲያ የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን ማረጋገጥ፣
- ሥራውን በቅርብ የሚከታተልና የአገር አቀፉ ካውንስል ኮሚቴ አባል የሚሆን ባለሙያ መመደብ፣
- የሲአርሲ ማስፈፀሚያ እቅድን ከመደበኛ የተቋም ዕቅድ ጋር መጣጣም ክትትል ማድረግና ማረጋገጥ፣
- የሲአርሲ ማስፈፀሚያ ሰነድ በተዋረድ ወደ ዲፓርትመንቶች መውረዱን ማረጋገጥ፣
- የአፈፃፀም ሪፖረት በየሩብ ዓመት የአገር አቀፉ ካውንስል ማቅረብና ቀጣይ አቅጣጫ እንዲሰጥ ማደረግ፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረግ የአገር አቀፉ ካውንስል ስብሰባ ላይ መሳተፍ፣
- በተቀመጠው የአፈፃፀም መለኪያ መሰረት መተግበሩን ማረጋገጥ፣
- የጤና የሰው ሀብት አመራርን ውጤታማነት ማረጋገጥ፣
- ለጤና ባለሙያዎች ሙያቸውን የሚተገብሩበት ምቹ የሥራ ቦታ መፈጠሩን ማረጋገጥ፣
- ሞዴል የጤና ባለሙያዎች መምህራንን መለየትና መምረጥ እንዲሁም በንቅናቄው ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የሲአርሲ አምባሳደሮችን መሰየም፣ ዕውቅና፣ መስጠትና መደገፍ፣
- ዓመታዊ የጤና ባለሙያዎች ቀን በማዘጋጀት የተሻለ የአፈጻጸም ውጤት ያስመዘገቡና ምሳሌ የሆኑ መምህራንን ዕውቅና መስጠትና መሸለም፣
- ህጋዊ አሰራሮችንና ፍሬምወርኮች መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
- የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች የሲአርሲ አተገባበር ባለቤትና ስፖነሰር መሆናቸውን ማረጋገጥ
- በጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎች የ ሲአርሲ ፅንሰ-ሀሳብ በቅድመ ሥራ የስልጠና ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ፣
- የጤና ሙያ ሰልጣኞች ሙያቸውን እንዲወዱ፣ እንዲያከብሩና የህዝብ አገልጋይነት ስሜት እንዲያዳብሩ ጥረት እንዲደረግ ማድረግ፣
- ከተማሪዎች ህብረትና የሜዲካል ተማሪዎች ማህበር ጋር ስለተፈፃሚነቱ በጋራ መስራት፣
- ደረጃውን የጠበቀ የሙያ ስነ-ምግባርና የሲአርሲ ትግበራን የሚከታተል ኮሚቴ ማዋቀርና መከታተል፣
- ሁሉም መምህራን የሲአርሲና የሙያ ስነ-ምግባር ሞዴል ስለመሆናቸው ማረጋገጥ፣

## 7.6 የ ክልል ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር እና ሚናና ተሳትፎ

## 7.7 የ ክልል ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር

1. የክልል ፕሬዚዳንት---------------------------------- የካውንስል ሰብሳቢ
2. የክልል ትምህርት ቢሮ ሃላፊ-----------------------የካውንስል ምክትል ሰብሳቢ
3. የክልል ጤና ቢሮ ሀላፊ ------------------------------የካውንስል ጸሐፊ

**የካውንስል አባላት**

4. የክልል ፖለቲካ እና የማህበረሰብ መሪዎች፣
5. የክልል ጤና አገልግሎት ተገልጋዮች፣
6. የክልል ጤና ተቋማት /የግልና የመንግሥት/ ተወካዮች
7. የክልል ቁጥጥር አካላት፣
8. የክልል ጤና ሥነ-ምግባር ኮሚቴዎች፣
9. የክልል ፍትህ አካላት፣
10. የክልል ሠብዓዊ መብት ተቋማት፣
11. የክልል ጤና ባለሙያዎች ማህበራት፣
12. የክልል ባለሙያዎች፣
13. የክልል ጤና ቢሮ ኤጀንሲዎች፣
14. የዞን እና የወረዳ ጤና ቢሮዎች ተወካዮች፣
15. የክልል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
16. ምልአተ ህዝቡ ፣
17. የክልል ህሙማን ማህበራት፣
18. የዞንና የወረዳ ትምህርት ቢሮዎች ተወካዮች፣

## 7.8 የክልል ሲአርሲ ካውንስል አባላት ሚናና ተሳትፎ

- የአገራዊ ንቅናቄውን ግብ በተዋረድ በክልል፣በዞን፣በወረዳና በቀበሌ መሳካት ማረጋገጥ፣
- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ ለክልል፣ለዞን፣ለወረዳና ለቀበሌ ምክርና አቅጣጫ መስጠት፣

- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ የክልሉን አመታዊና እስትራቴጂክ እቅዶችን ማውጣትና ማጽደቅ፣
- በየሩብ አመቱ የክልል ካውንስል አባላት ስብሰባ ማድረግ፣
- የሩብ አመቱን፣ የግማሽ ዓመትና የዓመት የክልሉን በአገራዊ ንቅናቄው ያለውን አፈጻጸም መገምገም፣
- በክልሉ ለንቅናቄው አመታዊ በጀት ማፀደቅ፣
- በየደረጃው ከዞን ፣ከወረዳና ከቀበሌ ካውንስል የሚመጡ ሪፖርት ማዳመጥና ምላሽ መስጠት፣
- በክልል ደረጃ ለሚከበሩ የሲአርሲ ቀን፤ የክልል አምባሳደሮች ምርጫ እና ስያሜ እንዲሁም ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ምክር መስጠት፣
- በክልሎች የንቅናቄውን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣
- በክልሎች ንቅናቄውን በቋሚነት መቆጣጠርና መገምገም፣
- በክልሎች በንቅናቄው ንቁ ተሳትፎ ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እውቅና እንዲሰጥ ማድረግ፣
- በክልሎች አገራዊ ንቅናቄውን በሚመለከት አመራርና አቅጣጫ መስጠት፣
- በክልሎች አገራዊ ንቅናቄውንን በባላይነት መምራት፣
- በክልሎች የአገራዊ ንቅናቄውን ትግበራ በየደረጃው በባላይነት ወጥነት ባለው መልኩ መቆጣጠር፣
- በክልሎች አገራዊ ንቅናቄውን የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ስራ መስራት፣

## 7.9 <u>የዞን ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር ሚናና ተሳትፎ</u>

### <u>የዞን ሲአርሲ ካውንስል አባላት ዝርዝር</u>

1. የዞን አስተዳዳሪ ------------------------------------ የካውንስል ሰብሳቢ
2. የዞን ትምህርት ሚኒስቴር ሃላፊ------------------ የካውንስል ምክትል ሰብሳቢ
3. የዞን ጤና ቢሮ ሀላፊ ------------------------------- የካውንስል ጸሐፊ

<u>የካውንስል አባላት</u>

4. የዞን ፖለቲካ እና የማህበረሰብ መሪዎች፣
5. የዞን ጤና አገልግሎት ተገልጋዮች፣
6. የዞን ጤና ተቋማት /የግልና የመንግሥት/ ተወካዮች
7. የዞን ቁጥጥር አካላት፣
8. የዞን ጤና ሥነ-ምግባር ኮሚቴዎች፣
9. የዞን ፍትህ አካላት፣
10. የዞን ሠብዓዊ መብት ተቋማት፣
11. የዞን ጤና ባለሙያዎች ማህበራት
12. የዞን ባለሙያዎች

13.የዞን ጤና ቢሮ ኤጀንሲዎች
14. የወረዳ ጤና ቢሮዎች ተወካዮች
15.የዞን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
16.ምልአተ ህዝቡ
17.የዞን ህሙማን ማህበራት
18.የወረዳ ትምህርት ቢሮዎች ተወካዮች

## 7.10የዞን ሲአርሲ ካውንስል አባላት ሚናና ተሳትፎ

- የአገራዊ ንቅናቄውን ግብ በተዋረድ በዞን፤በወረዳና በቀበሌ መሳካት ማረጋገጥ
- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ ለዞን፤ለወረዳና ለቀበሌ ምክርና አቅጣጫ መስጠት
- በንቅናቄው አተገባበር ዙሪያ የዞኑን አመታዊና እስትራተጂክ እቅዶችን ማውጣትና ማጽደቅ
- በየሩብ አመቱ የዞኑን ካውንስል አባላት ስብሰባ ማድረግ
- የሩብ አመቱን የግማሽ አመትና የአመት የዞኑን በአገራዊ ንቅናቄው ዙሪያ ያለውን አፈጻጸም መገምገም
- የዞኑን ለንቅናቄው አመታዊ አቅድ ማውጣት
- የዞኑን ለንቅናቄው አመታዊ በጀት ማጽደቅ
- በየደረጃው ከዞን ፤ከወረዳና ከቀበሌ ካውንስል የሚመጡ ሪፖርት ማዳመጥና ምላሽ መስጠት
- በዞን ደረጃ ለሚከበሩ የሲአርሲ ቀን፤ የዞን አምባሳደሮች ምርጫ ናስያሜ እንዲሁም ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ምክር መስጠት
- በዞኑ የንቅናቄውን ቀጣይነት ማረጋገጥ
- በዞን የንቅናቄውን በቋሚነት መቆጣጠርና መገምገም
- በዞኑ በንቅናቄው ንቁ ተሳትፎ ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እውቅና እንዲሰጥ ማድረግ
- በዞኑ አገራዊ ንቅናቄውን በሚመለከት አመራርና አቅጣጫ መስጠት
- በዞኑ አገራዊ ንቅናቄውንን በባላይነት መምራት
- በዞኑ የአገራዊ ንቅናቄውንትግበራ በየደረጃው በባላይነት ወጥነት ባለው መልኩ መቆጣጠር፣
- በዞኑ አገራዊ ንቅናቄውን የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ስራ መስራት፣

## 8. የ ሲአር ሲ ትግበራ አፈፃፀም ማመላከቻ (Indicators)

የዚህ ንቅናቄ ዋና አላማ በጤናው ዘርፍ የተቀመጡትን የተለጠጡ ግቦች ከማሳካት አንፃር የጤና ባለሙያው ቁልፍ ሚና የሚጫወትበት ቁመና ላይ ማድረስ ነው፡፡ በተለይም ጥራቱ የተጠበቀ እና ፍትሀዊ የጤና አገልግሎት ግቦችን ለማሳካት ንቅናቄው ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡የዚህ ንቅናቄ የስኬት መለኪያዎች በዋነኝነት በዘርፉ የተቀመጡ የልማት ግቦች በአስተማማኝነት ሲሳኩ ነው፡፡ ስለሆነም የንቅናቄውን ውጤት ሊለኩ የሚችሉ ከዋና ዋና የጤና ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ የአፈፃፀም መለኪያ መዘርዝር (matrix) በማዘጋጀት እያንዳንዱ የጤና ተቋም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚያስችል ሥርአት ይዘረጋል፡፡ በተቋም ደረጃ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚወዳደሩበት መሥፈርት በማዘጋጀት ጤናማ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር መሥራት ይገባናል፡፡በዚህ መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የ ሲአርሲ ትግበራ አፈፃፀም ማመላከቻ አፈጻጸሙን ለመገምገም የሚጠቅሙ ይሆናል፡፡

- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ የግልና የመንግስት የጤና ተቋማት ቁጥር(80%)
- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር(90%)
- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ የጤና ባለሙያዎች ማህበራት ቁጥር (90%)
- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ የጤና ሳይንስ ኮሌጆችና ዩኒቨርቲዎች ቁጥር(90%)
- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ የህሙማን ማህበራት ቁጥር(90%)
- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር(90%)
- አገራዊ ንቅናቄውን ተግባራዊ ያደረጉ የግል የጤና ተቋማት ቁጥር(90%)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ ስልጠና የወሰዱ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር(90%)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ የተሰሩ የማስተዋወቅ ስራዎች የወሰዱ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር(90%)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ ስልጠና የወሰዱ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቁጥር(90%)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ በአገር አቀፍ ካውንስሉ የተደረጉ ስብሰባዎች(4/በአመት)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ በክልል ካውንስሉ የተደረጉ ስብሰባዎች(4/በአመት)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ በዞን ካውንስሉ የተደረጉ ስብሰባዎች(4/በአመት
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ በወረዳ ካውንስሉ የተደረጉ ስብሰባዎች(4/በአመት)
- በአገራዊ ንቅናቄውን ዙሪያ የቅድመ ስራ ስልጠና የወሰዱ ተማሪዎች ቁጥር(3000/በአመት)
- በአገራዊ ንቅናቄው ዙሪያ የተመረጡ አምባሳደሮች ብዛት(15/በአመት)
- የህሙማንን እርካታ ወደ 90%ማሳደግ፣
- የባለሙያ ፍልሰትን በ 20% መቀነስ፣

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚ አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 1 | የማስተግበሪያ ሰነድ ዝግጅት ማጸደቅ | | x | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | የአገር አቀፉን ፤የክልል ፤የዞን፤ የወረዳ የሲአርሲ ካውንስል ማቋቋም | | | x | x | | | | | | | | | | | |
| 3 | የነባሪዊ ሁኔታ ግምገማ | -የጤና ባለሙያዎች ሙያቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ ማነቆ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች መተንተን<br><br>-በማህበረሰቡ ዘንድ በጤና አገልግሎትና ሙያተኞች ላይ የሚታየውን የተዛባ አስተያየት ነቅሶ ማውጣት፣ | | x | x | | | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚ አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| | | -የማነቆ ትንተና በየደረጃው መፈጸም፣<br><br>-በተለዩት ችግሮች ላይ የጋራ መተማመን መድረስ፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | የ ሲአርሲ ንቅናቄን በይፋ ማስጀመር፣ | -ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በ ESEA አዳራሽ በይፋ ማስጀመር፣<br><br>-ሁለተኛ ዙር የ ሲ አርሲ ንቅናቄ በይፋ ማስጀመር በ ጥቁር አንበሳ ሆ/ል እና በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ባለሙያዎች በተገኙበት በይፋ ማስጀመር፣ | | | | | | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክአርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 5 | በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የስነ ምግባር ትምህርት ለሚሰጡ መምህራን የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት እና የተማሪዎች የጤና ክበባት እንዲጠናከሩ መስራት፣ | በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ትምህርት የሚሰጠው የሲቪክስና የግብረገብ ትምርት እንዲጠናከር ለማድረግ ስልጠና ማዘጋጀት፣ | | | | X | x | | | | | | | | | |
| 6 | ወደ ጤና ትምህርት ለሚገቡ ተመልማዮች ስለሚገቡበት የሙያ ዘርፍ ምክር መስጠት፣ | | | | | X | x | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| **7** | የጤና ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት እና ስርአተ ትምህርት በሲአርሲ እንዲቃኝ ማድረግ | -መምህራንን በሲአርሲ ማብቃትና ለተማሪዎቻቸው አርአያ እንዲሆኑ ለማስቻል ተከታታይ ስልጠናዎች እንዲወስዱ ማድረግ፣ | | **x** | **x** | | | | | | | | | | | |
| | | -መምህራን በሲአርሲ ተቃኝቶ በሚዘጋጀው ካሪኩለም ዙሪያ እንዲሰለጥኑና ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡<br><br>-ሻምፒዎንስ ለሆኑ መምህራን እውቅና መስጠት፡፡ | | | | | | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚ አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| | የጤና ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት እና ስርአተ ትምህርት በሲአርሲ እንዲቃኝ ማድረግ | -መምህራን በሲአርሲ ተቃኝቶ በሚዘጋጀው ካሪኩለም ዙሪያ እንዲሰለጥኑና ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ።<br><br>-ሻምፒዎንስ ለሆኑ ተማሪዎች እውቅና መስጠት።<br><br>-ስርአተ ትምህርተ በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለተማሪዎች የሚሰጡ Ethics and professionalism course ካሪኩለምእንዲፈተሽ በማድረግ ወጥ የሆነ ሀገር አቀፍ ካሪኩለም እንዲኖር ማድረግ። | x | x | | | | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| | | -በሚቀረጸው በሲአርሲ ካሪኩለም ውስጥ ሌሎችን ማካተት፣<br><br>-በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያለው የተማሪዎች ተከታታይ ምዘና ስርዓት ከእውቀትና ክህሎት መለካት ባሻገር አመለካከትን (Attiude) ማካተቱን ማረጋገጥ፣ | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | የጤና ባለሙያዎች ቅድመ ስራ ስነ ምግባር ምዘና ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ | -የሙያ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ማጠናከርና የሙያ ፍቃድ አሰጣጡ የሲአርሲ መርሆችን ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ፣<br><br>-የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች በሲአርሲ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ማድረግ፣ | | | | | x | x | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 9 | በጤና ተቋማት ውስጥ የሙያ ስነ ምግባር ቀጣይነት ማረጋገጥ (ሲአርሲ) | -የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ማጠናከር፣<br>-የሙያ ስራ ወሰን (Scope of Practice) ተግባራዊነቱን ማጠናከር፣<br>-በተቋ ማት ውስጥ የሲአርሲ ትግበራና ማሻሻያ ኮሚቴ በማቋቋም ተግባራዊ ማድረግ፣<br>-አርአያ ለሚሆኑ ባለሙያዎች የማበራታቻ ስርዓት መዘርጋት፣<br>-በየተቋማቱ የስነምግባር ማዕከል ማቋቋም፣ | | x | x | | | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 10 | የሙያ ማህበራት በንቅናቄው የባለቤትነት ድርሻውን እንዲወስዱ ማድረግ | -የማህበራቱን የአባላት ቁጥራቸውን መጨመር፣<br>-ማህበራቱ ተደራሽነታቸውን እንዲያሰፉ ማገዝ፣<br>-በዚህ ንቅናቄ ማህበራቱ በዕቅድ የተመሠረተ ድጋፍ የሚሠጡበት ሁኔታ ማመቻቸት፣<br>-ቡድናዊ ግምገማና የውይይት ባህል እንዲያዳብሩ የሙያ ማህበራቱ የበኩላቸውን በጎ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣ | | | | | | x | x | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 11 | የንቅናቄ አምባሳደሮች በመሰየም ንቅናቄውን ማጠናከር፣ | -በአገር ደረጃ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በጤና ተቋም ውስጥ በጥሩ ሥነ ምግባራቸው እና ሕዝብን በቅንነትና በታማኝነት ያገለገሉ እና በማገልገል ላይ ያሉ ባለሙያዎችን በአምባሳደርነት መሰየም፣<br>-የሚጫወቱትን ሚና በዝርዝር በማስቀመጥ በጋራ መዘጋጀት፣<br>-የእነዚህን ባለሙያዎች ተሞክሮ ቀምሮ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ማስተላለፍ፣ | | | | | | x | x | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 12 | የጤና ባለሙያዎች መረጃ አያያዝ ስርዓት በኤሌትሮኒክስ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ | | | | | | | x | x | x | | | | | | |
| 13 | የገፅታ ግንባታ | -የህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ሥራዎችን በሠፊው መስራት፣<br><br>-በተለይም በዕለት ተዕለት በጤና ባለሙያዎች የሚሠሩ በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ ሊሠጡ የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት ለህዝቡ ማስተዋወቅ፣<br><br>-የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የጤና ተቋማትን የሚጎበኙበት እና ለሙያው ፍቅር እንዲያሣድሩ የተቀናጀ ፕሮግራም በመቅረጽ መተግበር፣ | | | | | | | | | X | x | X | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚ አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| | | -የህዝብ ግንኙነትና የኮሙኒኬሽን ስራ በመስራትና ንቅናቄውን የማስተዋወቅ ስራ በስፋት በመስራት በህብረተሰቡ አምነት የሚጣልበት የህክምና አገልግሎት መፍጠር፣<br><br>-ለአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤ/ት ተማሪዎች የተቀናጀ ፕሮግራም በመቅረጽ የተመረጡ ሞዴል የጤና ተቋማትን እንዲጎበኙ በማድረግ ለሙያው ፍላጎት እንዲኖራቸው ማድረግ፣<br><br>-ያሉትን የሚዲያ ተቋማት በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራዎች በዘመቻ በሰፊው መጀመር፣ | | | | | | | | | X | x | X | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| | | -በየጤና ተቋሙ የሚሠጡ የጠዋት የጤና ትምህርቶችን ጥራት ያለው አገልግሎት እና የታካሚን ክብር በጠበቀ መልኩ እንዲሠጥ ማድረግ፣<br><br>-በየጤና ተቋሙ አስተዳደር ቦርድ ውስጥ የሚሣተፉ የህብረተሰብ ወኪሎችን አቅም በማሣደግ ንቅናቄው በየተቋሙ ሣይቀዛቀዝ መቀጠሉን እንዲከታተሉ ማብቃት፣<br><br>-በጥሩ ሥነ-ምግባር የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን በህብረተሰቡ ዕውቅና እንዲሠጣቸው ማመቻቸት፣ | | | | | | | | | | | | | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚ አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 14 | ምልዓተ ሕዝቡን የንቅናቄው አካል ማድረግ፣ | -ተገልጋዩ ሕዝብ በጤና ላይ ያለውን ግንዛቤ ማሣደግና መብቱንና ግዴታውን የሚጠይቅ እንዲሆን ማድረግ፣<br><br>-ተገልጋዩ ሕዝብ የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ጥራቱን የጠበቀና የተሟላ የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል፣<br><br>-መብቱን የሚጠይቅና የሚሟገት ማህበረሰብ ለመፍጠር የጤና ልማት ሠራዊ አደረጃጀትን በዚህ ዙሪያ በሰፊው ማነቃነቅ፣<br><br>-በየጤና ተቋማቱ የሚካሄደው የህዝብ ክንፍ ስብሰባን ተቋማዊ በሆነ መልኩ ማስኬድ፣<br><br>-በጤና ተቋም ከሕዝቡ የሚሠጠውን አስተያየት በመውሰድ የአገልግሎት አሠጣጡ የሚሻሽልበትን ስርአትመዘርጋት፣ | | | | | | | | x | X | x | x | x | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 15 | በጤና ሣይንስ ትምህርት ቤቶች ንቅናቄውንማስተዋወቅና መተግበር፣ | -የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን በአገራዊ ንቅናቄው ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣<br>-ተማሪዎች ሙያቸውን እንዲወዱና እንዲያከብሩ ብሎም ህብረተሰቡን የማገልገል መንፈስ እንዲያዳብሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣<br>-ከተማሪዎች ህብረትና ከህክምና ተማሪዎች ህብረት ጋር በጋራ መስራት፣ | | | | | | | x | x | X | x | x | x | | |

| | ስትራቴጂክእርምጃ፣ | ዋናዋናተግባራትናተግባራት | የጊዜሰሌዳ | | | | | | | | | | | | ፈጻሚአካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | | |
| 16 | የሲአርሲትግበራ ክትትልና ግምግማ ስርዓት መዘርጋት፣ | - የቅሬታአቀባበል፣ምርመራና እርምጃ አወሳሰድ ስርዓት መዘርጋት፣<br>-የሲአርሲ ትግበራ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፣ | | | | | | | | x | x | x | x | x | | |
| **17** | ከአገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ ተቋማት የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣ | -ለንቅናቄው መሳካት ከአገር ውስጥና ከአለም አቀፍ ተቋማት የልምድ ልውውጥና የተሻለ ተሞክሮን መውሰድ፣ | | | x | x | x | | | | | | | | | |